
EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 4

## ኪነ-ጥበብ እና ቀለም

PK3



AppleTree

EVERY CHILD READY @Home

# Unit 4

## ኪነ-ጥበብ እና ቀለም

AppleTree

©2020
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ከዚህ በታች በቅጂ መብት የተያዙትን መብቶች ሳይገድብ ፣ የትኛውም የዚህ ህትመት ክፍል  እንደገና ሊባዛ ፣ ሊከማች ወይም ወደ ሌላ የማስመለሻ ስርዓት ሊተላለፍ አይችልም  ፣ ወይም በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ (ኤሌክትሮኒክ ፣ ሜካኒካል ፣  ፎቶ ኮፒ ማድረግ ፣ መቅዳት ወይም በሌላ መንገድ) ያለ ቅድመ የጽሁፍ ፈቃድ ።

AppleTree Institute for Education Innovation
1801 Mississippi Ave SE, 3rd Floor
Washington, DC 20020

የቅጂ መብት © 2020 ጽሑፍ እና ስዕሎች። AppleTree Institute(አፕል ትሪ ኢንስቲትዩት) መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# PK3 ክፍል 4 አጠቃላይ እይታ



**ውድ ቤተሰቦች,**

ወደ ክፍል 4 እንኳን በደህና መጡ! ክፍል 4 በጠቅላላ ስለ ኪነ-ጥበብ እና ስለ ቀለም ነው! ልጅዎ ስለተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዓይነቶች እና ስለ መጀመሪያ እና ሁለተኛ ቀለሞች ይማራል!

## ክፍል 4 መጽሐፍት




- *(Artists Create! ) አርቲስቶች ይፍጠሩ!* በ (Akiea Gross) አኪያ ግሮስ
- *(Sorting) መደርደር* በ (Ruth Ebisuzaki & Beryl Salinger Schmidt) ሩት ኤቢሱዛኪ እና በሪል ሳሊንገር ሽሚት
- *(Party Plans ) የፓርቲ ዕቅዶች* *በ* (Corinne Fennelly) ኮርኔ ፊነሊ
- *(Rafael's Alley) የራፋኤል አሌይ* በ (Livy Traczyk) በሊቪ ትራሲክ

*ECR @ የቤት ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታሉ: በተለያዩ መንገዶች መቀባት ፣ ቅርፃ ቅርጾችን መስራት ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት እና ጭፈራ። ልጅዎ እንዲሁ 5 ነገሮችን ይቆጥራል ፣ ስለ ድብልቅ ቃላት ይማራል እንዲሁም ተመሳሳይ ድምፅ ማውጣትን / መግጠምን ይለማመዳል!*

## ክፍል 4 የቃላት ዝርዝር

- ኪነ-ጥበብ
- አርቲስት
- የቀለም ብሩሽ
- የመጀመሪያ ቀለም
- ቀስተ ደመና
- ሁለተኛ ቀለም
- ቅርፃ ቅርፅ
- ቀለም


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሳምንት 1


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 አጠቃላይ እይታ

## ኪነ- ጥበብ እና አርቲስት



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ ይህንን ያደርጋል፡

ይማራሉ፡- ስለተለያዩ የአርቲስት አይነቶች፣ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ቀለሞች፣ 5 እቃዎችን መቁጠር እና ስለ ድብልቅ ቃላት መማር።

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



## አርቲስት

እንደ ሥዕሎች ያሉ ኪነ-ጥበቦችን የሚሠራ ሰው ወይም በሰዎች ፊት የሚተውን ሰዉ እንደ ዳንሰኞች እና ዘፋኞች



## የመጀመሪያ ቀለም

ሌሎች ቀለሞችን ሁሉ ለመሥራት ሦስት ቀለሞች ፡- ቀይ ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ ግልጋሎት ላይ ይውላሉ



## ሁለተኛ ቀለም

የመጀመሪያ ቀለሞችን በማቀላቀል የተሠሩ ቀለሞች


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

አስብበት!

በዚህ ሳምንት ስለተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዓይነቶች ይማራሉ። ፓኬቱን ከመጀመርዎ በፊት የበለጠ ማወቅ ስለሚፈልጉት የኪነ-ጥበብ ዓይነት ይጻፉ እና ይሳሉ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ



## **STEM:** በጣት እስከ **5** መቁጠር

- ልጅዎ በጣቶቹ እንዲቆጥር ያስተምሩት። ይህን ይበሉ፣ **በጣቶቻችን እንቁጠር።** እጅትን ጨብጠው ያሳዩት እና ይህን ይበሉ፣ **ወደላይ የተዘረጉ ጣቶች የሉም ማለት ዜሮ ማለት ነው ።**
  - **1** - ጠቋሚዎን ጣትዎን ያውጡ
  - **2** - ጠቋሚውን እና የመሃል ጣትዎን ያውጡ
  - **3** - ሶስቱን የመሃል ጣቶችዎን ያውጡ
  - **4** - አራት ጣቶችዎን ያውጡ (አውራ ጣት አይደለም)
  - **5** - ሁሉንም ጣቶች ያውጡ እና አውራ ጣትንም
- ይህን ይበሉ, **አሁን ከኔጋ ቁጠር።** በጋራ ለሁለት ጊዜ ያህል በጣትዎ ይቁጠሩ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት**:** የሚወዱትን ቀለም በማጣበቅ ኮላጅ ማድረግ

**ቁሳቁሶች: ከለሮችs, ቴፕ ወይም ግሉ, ወረቀት, መፅሔቶች, በራሪ ወረቀቶች, ለልጆች የሚሆኑ መቀሶች (ወይም አስቀድመው ለልጅዎ ስዕሎችን ይቁረጡ)**

- ይጠይቁ, **የምትወደው ቀለም የቱ ነው?** ስለዚያ ቀለም ስለሆኑ ነገሮች በጋራ ይወያዩ ።
- ይህን ይበሉ፣ **አንተ የምትወደውን ቀለም የሆኑ ነገሮችን እንዲጣበቁ / ኮላጅ ልታደርግ ነው ።**
- ልጅዎ እራሱን  ምስሎችን ወይንም የሚወዱትን ቀለም ያላቸውን ስዕሎች በመሳል በቴፕ በመጠቅለል / በማጣበቅ ኮላጅ እንዲሠራ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ኮላጅህ / ስለ ተጣበቀው ነገር ንገረኝ። ምን ሥዕሎች ተጠቅመሃል?**



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 ቀን 1

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የተዋሃዱ / ኮምፓውንድ ቃላት

**ቁሳቁሶች**: **የተዋሃዱ / ኮምፓውንድ ቃላት 1**




- ይህን ይበሉ, **የተዋሃዱ ቃላት አዲስ ቃል ለመስራት አንድ ላይ የተቀመጡ ሁለት ቃላት ናቸው ።**
- ለ "cupcake/ ካፕኬክ." ለልጆ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: cup / ካፕ** (ለአፍታ አቁም) **cake/ ኬክ. እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው የካኘኬክ ሥዕሉን ያሳዩ) **cupcake / ካፕኬክ!**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **cup / ካፕ** (ለአፍታ አቁም) **cake/ ኬክ.** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የካፕኬክ ሥዕሉን ያሳዩ ። **Cupcake/ ካፕኬክ!**
- ለ snowball/ ስኖቦል ይድገሙ። ሌሎቹን ስዕሎች በዚህ ሳምንት ወደ በኋላ ለሚገኘው እንቅስቃሴ ይሆኑ ዘንድ ያስቀምጧቸው።

## አንብብ: (*Artists Create*) አርቲስቶች ይፍጠሩ!

**ቁሳቁሶች**: *(Artists Create! ) አርቲስቶች ይፍጠሩ!*


- አንብብ (*Artists Create*)*አርቲስቶች ይፍጠሩ!* ከልጆ ጋር
- በኋላ, በመጽሐፉ ውስጥ ስለ ተለያዩ የአርቲስቶች አይነቶች በጋራ ይነጋገሩ። አንዱን ዓይነት ይምረጡ እና ልጅዎ ያንን አርቲስት መሆን ምን ሊመስል እንደሚችል እንዲያስብ ይጠይቁት ። ለምሳሌ, ይህን ይጠይቁ, **የባሌት ዳንስ መደነስ ምን አይነት ስሜት ሊኖረው የሚችል ይመስልዎታል?**




አርቲስቶች ይፍጠሩ!
የተፃፈው በአኪያ ግሮስ ምስል በብሪይ ዋከር


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስኖ



ቦል




ስኖቦል



ኩፕ



ኬክ



ኩፕኬክ




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።





ሃውስ

ቦት




ሃውስቦት





ፓን

ኬክ



ፓንኬክ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ፊዲ።



ቦል



ፉት



ፉትቦል



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።


# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 ቀን 2

## STEM: የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ቀለሞች

**ቁሳቁሶች**: [የቀለም ተሽከርካሪ](#) [ቀለም የሌለው ተሽከርካሪ](#), **ከለሮች**


- ይህን ይበሉ, **የቀለም ተሽከርካሪውን በመጠቀም ስለ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቀለሞች እንማር ።**
- **የመጀመሪያ ቀለሞች ሌሎች ቀለሞችን ለማግኘት አንድ ላይ የምንደባለቅባቸው ቀለሞች ናቸው ። ቀይ ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ የመጀመሪያ ቀለሞች ናቸው ።** በቀለም ሽክርክሪት ላይ ወደ እነሱ ይጠቁሙ። **P /ፒ ፊደልን በሚያዩበት ወረቀትዎ ላይ ቀለሞቹን ይቀቡ።**
- **አሁን S/ኤስን በሚያዩበት ስፍራ ላይ ሁለተኛ ቀለሞች ይቀቡ። የመጀመሪያ ቀለሞችን ስናቀላቅል ሁለተኛ ቀለሞችን እናገኛለን። ቀይ እና ሰማያዊ ስናቀላቅል ሐምራዊ ቀለምን እናገኛለን። ስለዚህ በቀይ እና በሰማያዊ መካከል ሐምራዊ ቀለምን ቀባ ።** ለብርቱካናማ (ቀይ እና ቢጫ) እና ለአረንጓዴ (ሰማያዊ እና ቢጫ) ይድገሙ።
- የታተመውን ፣ የቀለም የተቀባውን የቀለም ተሽከርካሪ በዚህ ክፍል ለሚገኙ እንቅስቃሴዎች ይሆን ዘንድ ያስቀምጡት።



## እራሱን የቻለ ትምህርት: ድንቅ ሥራን መቅረጽ

**ቁሳቁሶች**: [የሊጥ መጫወቻ](#), [Artists Create!/አርቲስቶች ይፍጠሩ!](#)

- ከልጆ ጋር፣ የ*Artists Create! / አርቲስቶች ይፍጠሩ ገፅ 11 & 14 ይመልከቱ !* እና እንደ ሐውልቶች እና የሸክላ ስራዎች ባሉ በሸክላ ሊፈጥሩ ወይም ሊቀርፆቸው ስለሚፈልጓቸው የቅርፅ አይነት ይናገሩ።
- ይህን ይበሉ, **እንደ ሸክላ፣ የሊጥ ጭቃው በመጠቀም አንድ የሚያምር ነገር መስራት ትችላለህ።**
- ልጅዎ እራሱን ችሎ በመጫወቻ ሊጡ አንድ ነገር እንዲሠራ ያድርጉት።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ፈጠርከው ነገር ንገረኝ !**


የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ እንነጋገር

- ይጠይቁ, **አርቲስት መሆን ምን አይነት ስሜት ያለው ይመስልሃል?**
- ልጅዎን 2-3 የሚሆኑ የመከታተያ ጥያቄዎችን ይጠይቁ እንደ, **ለምን ይመስልሃል?** ወይንም, **ሌላ ምን የሚያደርጉ ይመስልሃል**? መልስ በመመላለስ ውይይት ማድረግን ተለማመዱ ::
- ስለ አርቲስት ስለመሆን ማውራት የማይፈልጉ ከሆነ ልጅዎን በምትኩ ስለ ምን ማውራት እንደሚፈልግ መጠየቅ ይችላሉ።


## የፅሁፍ ሃሳብ፡ እኔ አርቲስት ነኝ

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, እኔ አርቲስት ነኝ ፣ የጆርናል ገፅ**





- ከልጅዎ ጋር ስለ አርቲስት አይነቶች እና ስለ ፈጠራቸው ኪነ- ጥበብ ይናገሩ ::
- ልጅዎ ራሱን ችሎ መሆን ስለሚፈልገው የኪነ-ጥበብ ባለሙያ አይነት እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ::
- በኋላ, ይጠይቁ, **ያንን አይነት አርቲስት ለምን መረጥክ? እንደዚያ ዓይነት አርቲስት መሆን ምን ስሜት ሊኖረው ይችላል ብለህ ታስባለህ?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማስሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: ________________

ምን ዓይነት አርቲስት መሆን ትፈልጋለህ?



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 ቀን 3

## STEM: እስከ 5 ድረስ ዶቶች መቁጠር

**ቁሳቁሶች**: [የነጥብ ካርዶች 0-5](), **ከለሮች, የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች እንደ የወረቀት ክሊፖች ወይም ጠጠሮች**



- ይህን ይበሉ, **በእያንዳንዱ ካርድ ላይ የሚገኙትን ነጥቦች እንቁጠራቸው።** ልጅዎ ሲቆጠር እያንዳንዱን ነጥብ እንዲነካ ይርዱት። የተቆጠረውን የመጨረሻ ቁጥር ይድገሙ። **አንድ ፣ሁለት ሦስት፣ አራት፣ አምስት። አምስት ነጥቦች አሉ።**
- ይህን ይበሉ ፣**ተመሳሳይ ብዛት ያላቸውን የወረቀት ክሊፓችን በነጥቦቹ ላይ እናስቀምጥ።** በሚቆጠሩበት ጊዜ የወረቀት ክሊፖቹን በነጥቦች ላይ እንዴት እንደሚያስቀምጡ ሞዴል ያድርጉ ። **እያንዳንዱን የወረቀት ክሊፕ ከአንድ ነጥብ ጋር በማመሳሰል እየቆጠርኩ ነው ። አንድ** (የመጀመሪያውን የወረቀት ክሊፕ በመጀመሪያው ነጥብ ላይ ያስቀምጡ) **፣ ሁለት ፣ ሶስት ፣ አራት ፣ አምስት! አምስት የወረቀት ክሊፖች አሉ!**
- ልጅዎ ከሌሎቹ ካርዶች ጋር ራሱን ችሎ እንዲቆጥር ያድርጉ ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: የምወዳቸውን ቀለሞች መቀባት

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች, ወረቀት**

- ይህን ይበሉ, **የምትወዳቸውን ቀለሞች መቀባት ትችላለህ።**
- ልጅዎ በሚወዳቸው ቀለሞች በመጠቀም የመረጠውን ሥዕል ራሱን ችሎ እንዲስል ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ሥዕልህ ንገረኝ። ምን ዓይነት ቀለሞችን ተጠቅመሃል? እነዚህን ቀለሞች ለምንድን ነው በአንተ ዘንድ ተመራጭ/ ተወዳጅ የሆኑት ?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።


# ረቡዕ



## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ቃላትን መመስረት

**ቁሳቁሶች**: [**የተደባለቁ ቃላቶች 1**]() **በዚህ ሳምንት ከዚህ በፊት**


- ይህን ይበሉ, **አንድ የተዋሃደ ቃል ለመስራት ሁለት ቃላትን በአንድ ላይ ማሰባሰብን እንለማመድ!**
- ለ “houseboat/ ሃውስቦት” ለልጆ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: house / ሃውስ** (ለአፍታ አቁም) **boat/ ቦት። እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው ሃውስቦት ሥዕሉን ያሳዩ) **houseboat / ሃውስቦት!**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **house / ሃውስ** (ለአፍታ አቁም) **boat/ ቦት።** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የሃውስ ቦት ሥዕሉን ያሳዩ ። **Houseboat/ ሃውስቦት! ታላቅ ስራ!**
- ለነዚህ ቃላት ይድገሙ: pancak /ፓንኬክ እና football/ ፉትቦል። ሁለቱን ቃላት ሲያቀናጁ የተዋሃደው ቃል ምን እንደ ሆነ እንዲናገር ልጅዎን ይጠይቁ ። እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም! ኣድናቆትዎን አብዝተው ይስጡት!



## አንብብ: (*Artists Create!* ) *አርቲስቶች ይፍጠሩ!*

**ቁሳቁሶች**: [*(Artists Create! ) አርቲስቶች ይፍጠሩ!*]()

- ከልጆ ጋር ያንብቡ (*Artists Create!*) *አርቲስቶች ይፍጠሩ!*
- በኋላ, ሁለታችሁም ስለምትወዷቸው የፈጠራ መንገዶች ከልጅዎ ጋር አብረው ይነጋገሩ። ይህን ይበሉ,**የእኔን የአእምሮ ምናባዊ ስዕል እና የፈጠራ ችሎዬን ለ ____ መጠቀም እፈልጋለሁ። የአእምሮህን ምናባዊ ስዕል እና የፈጠራ ችሎታህን ምንን ለማድረግ ብታውለው ትወዳለህ?**




አርቲስቶች ይፍጠሩ!
የተፃፈው በአኪያ ግሮስ ምስል በብሪይ ዋከር


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 ቀን 3

## እንቀሳቀስ፡ የለበስከው ልብስ ከሆነ...

**ቁሳቁሶች:** ***አማራጭ - ሙዚቃ***


- ይህን ይበሉ, **ጨዋታ እንጫወት፡፡ የሆነ የቀለም አይነትን ከለበሱ ሊያደርጉዋቸው የሚችሉትን የተለያዩ ድርጊቶችን እጠራለሁ ፣ ስለዚህ ያንን ቀለም ለብሰው ከሆነ ያዳምጡ፡፡**
- የተለያዩ ድርጊቶችን ይዘዙ፣ ለምሳሌ ፣ **ቀይ ሸሚዝ ከለበሱ ወደላይ እና ወደ ታች ይዝለሉ ፣ ወይም ቢጫ ካልሲዎችን ከለበሱ ጣቶችዎን ያሽከርክሩ፡፡**
- ሚናዎችን ይቀይሩ እና ልጅዎ የተለያዩ ድርጊቶችን እንዲያዝ ይፍቀዱለት፡፡


## በጋራ መማር፡ የኛ የቁም ስዕል /ፖርትሬት


**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች, ወረቀት**


- ይህን ይበሉ, **እራሳችን አርቲስቶች በማድረግ እናም አንዳችን የአንዳችንን የፊት ፓርትሬት / የቁም ስዕል እንሰራለን ፡፡ ጥሩ ሥራ! ወይም ቀጥል! እየተባባልን አንዳችን አንዳችንን ማበረታታት እንችላለን!**
- ሌላኛው ቀለሞች በሚቀባበት ወቅት እርሶ በተመሳሳይ ጊዜ ወይም ተራዎን ጠብቀው ቀለም መቀባት ይችላሉ ፡፡ አብዝተው አድናቆትን ይግለፁ ፣ **በጣም ጠንክረህ እየሰራህ ነው!**
- በኋላ, ስለ ፓርትሬት / የቁም ስዕል አንድ ላይ ተነጋገሩ ፡፡


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።












©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።







©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 ቀን 4

## STEM: ቀለሞችን መቀላቀል

**ቁሳቁሶች**: **[የቀለም ተሽከርካሪ ፣ ቀለም የሌለው ተሽከርካሪ](#) ፣የውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች**



- ከልጅዎ ጋር የቀለሙን ተሽከርካሪ በመጠቀም የመጀመሪያ (ቀይ ፣ ቢጫ ፣ ሰማያዊ) እና ሁለተኛ (ሐምራዊ ፣ ብርቱካናማ ፣ አረንጓዴ) ቀለሞችን ይከልሱ ።
- ይህን ይበሉ,**ባዶውን የቀለም ተሽከርካሪ ትሞላለህ እና የመጀመሪያዎቹን ቀለሞች በማደባለቅ ሁለተኛ ቀለሞችን አዘጋጅ።**
- በመጀመሪያ፣ ልጅዎ  ቦ/ፒን በሚይበት ቦታ ላይ የመጀመሪያዎቹን ቀለሞች እንዲስል ያድርጉ ።
- ከዚያ ብርቱካናማን ለመሙላት ቀይ እና ቢጫን ይቀላቅሉ እና ለአረንጓዴ (ሰማያዊ እና ቢጫ) እና ሐምራዊ (ሰማያዊ እና ቀይ) ይድገሙ ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: የመርጨት ኪነ- ጥበብ

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, የውሃ ቀለም የተቀባ ቀለም በውሀ የቀጠነ, የወረቀት ፎጣ ፣ የወረቀት ግማሹን በመጠምዘዝ ብሩሽ በማድረግ እና ጫፉን በቴፕ ወይም በጎማ / በራበር ማሰሪያ በመጠቅለል እጀታ መፍጠር**

- ይህን ይበሉ, **የወረቀት ፎጣዎን ወደ ቀለሙ ውስጥ በመንከር ከዚያም የመርጨት ኪነ-ጥበብን ለመስራት በወረቀትዎ ላይ ቀለሙን መርጨት ይችላሉ።** ለልጅዎ አንድ ጊዜ ያሳዩት።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ የራሱን የርጭት ሥዕሎች እንዲሠራ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ሥዕልህ ንገረኝ። ይህንን ዲዛይን ለምን መረጥክ?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 ቀን 4

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ እኔ ትንሹ የሻይ ማንቆርቆሪያ ነኝ

**ቁሳቁሶች**: [እኔ ትንሹ የሻይ ማንቆርቆሪያ ነኝ]

- ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላት ማዳመጥ ተለማመድ ይህን ይበሉ, **ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላት ወደ መጨረሻ ላይ ተመሣሣይ ድምፅ ይሰጣሉ, እንደ hop / ሆፕ እና pop/ፖፕ። ዘፈን እንዝፈን እና ተመሳሳይ ድምፅ የሚሰጡ ቃላትን እናዳምጥ ።**
- በጋራ, ዘፈኑን ዝፈኑ ወይንም እንደ ግጥም አንቡት ። ይህን ይበሉ ፣ **መጨረሻ ላይ ተመሳሳይ የሆኑ አንዳንድ ቃላትን ሰማሁ ። Stout /ስታውት እና spout/ስፓውት**
- ዘፈኑን በዝግታ ይዝፈኑ, አንድ ቨርስ አንድ ጊዜ ብቻ። ከእያንዳንዱ ቨርስ በኋላ ይህን ይጠይቁ, **የትኞቹን ተመሣሣይ ድምፅ ያላቸውን ቃላቶች ሰምተሃል?** (stout/ ስታውት -spout/ስፖውት -shout /ሻውት -out / አውት, true / ትሩ -do /ዱ, spout/ስፖውት -out / አዉት). ልጅዎ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ቃላትን ለመለየት የሚቸግረው ከሆነ ፣ ችግር የለውም። አሁንም እየተማረ ነው! ቃላቱን ለይለት።


**እኔ ትንሹ የሻይ ማንቆርቆሪያ ነኝ**

ኣይ አም ሊትል ቲ ቦት

ሻውት ኤንድ ታውት ሂር ኢዝ ማይ ሃንድል

ሂር ኢዝ ማይ ስፖውት ኹኤን አይ ጌት ኣል ስቲምድ አፕ

ሂር ሚ ሻውት

ቲፕ ሚ ኦቨር ኤንድ ፓር ሚ አዉት!

አይ አም ኤ ቬሪይ ስፔሻል ቲፓት


የስ ኢት ኢዝ ቬሪ ትሩ

ሂር ኢዝ አን ኤግዛምፕል ኦፍ ሁአት አይ ካንዱ
አይ ካን ተርን ማይ ሃንድል ኢንቱ ኧ ስፖውት
ቲፕ ሚ ኦቨር ኤንድ ፖር ሚ አዉት!

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የእኔ ፈጠራ


**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የኔ ፈጠራ የጆርናል ገፅ**

- ከልጅዎ ጋር ስለተለያዩ የኪነ -ጥበብ ዓይነቶች እና ፈጠራዎች ይነጋገሩ።
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ምን መፍጠር እንደሚፈልግ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ምን መፍጠር ትፈልጋለህ? እንዴት ትፈጥረዋለህ?**






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# እኔ ትንሹ የሻይ ማንቆርቆሪያ ነኝ

ኣይ አም ሊትል ቲ ቦት



ሻውት ኤንድ ታውት ሂር ኢዝ ማይ ሃንድል

ሂር ኢዝ ማይ ስፖውት ኹኤን አይ ጌት ኣል ስቲምድ አኘ

ሃሮ ማ ሻጡት

ቲፕ ሚ ኦቨር ኤንድ ፓር ሚ አዉት!

አይ አም ኤ ቬሪይ ስፔሻል ቲፓት

የስ ኢት ኢዝ ቪሪ ትሩ

ሂር ኢዝ አን ኤግዛምፕል ኦፍ ሁኦት ኣይ ካንዱ
አይ ካን ተርን ማይ ሃንድል ኢንቱ ኧ ስፖውት
ቲፕ ሚ ኦቨር ኤንድ ፖር ሚ አዉት!



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: ________________

ምን መፍጠር ትፈልጋለህ?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ



## STEM: ነገሮችን መቁጠር

**ቁሳቁሶች: የቤት ቁሳቁሶች እንደ ከለሮች ወይም ወረቀት ክሊፖች**

- ይህን ይበሉ, **አንድ ላይ እንቁጠረው ፡፡**
- ሲቆጥሩ 5 ነገሮችን ወደታች ያኑሩ እና እያንዳንዱን ነገር ይንኩ። ይህን ይበሉ ፣ **1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 ፣ 5 ፡፡ 5 ነገሮች አሉ።**
- በ 1 እና 5 መካከል መካከል ያሉ ነገሮች ያሳዩት እና ልጅዎ እንዲቆጥራቸው ይጠይቁት። ከዚያ ይጠይቁ, **ሁሉም በአንድ ላይ ስንት ናቸው?** ድምሩን / የመጨረሻውን ሳይናገር እንደገና ቢቆጥር ፣ የተናገው የመጨረሻው ቁጥር የነገሮችን አጠቃላይ /ድምር ቁጥር እንደሚወክል ልጁ እንዲገነዘብ መርዳት ይችላሉ ፡፡ **___ ነገሮች አሉ ፡፡**

## Independent Learning: Art Tools Matching

**ቁሳቁሶች:** [የኪነ-ጥበብ መሳሪያዎችን ማዛመድ](#) **(ቆርጦ ማውጣት)**

- አርቲስቶች ሊጠቀሙባቸው ስለሚችሏቸው የተለያዩ መሳሪያዎች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ይህን ይበሉ, **መሣሪያዎቹን በአንድ ላይ አጣምር ፡፡** 3-4 ጥንድ ካርዶችን ፊታቸውን ወደታች ገልብጥ ፡፡ ልጅዎ 2 ካርዶችን መገልበጥ አለበት። ካርዶቹ ከተመሳሰሉ ጥንዱን መያዝ ይችላሉ። ካልተመሳሰሉ ካርዶቹን መለወጥ እና እንደገና መሞከር ይችላሉ።
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ጨዋታውን ማጠናቀቅ ይችላል።
- በኋላ, መሣሪያ ይምረጡ እና ይጠይቁ, **አንድ አርቲስት ይህንን እንዴት ይጠቀማል?**





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 1 ቀን 5

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ህትመት እና ስዕሎች


**ቁሳቁሶች**: **ስዕሎች ወይም  ምስሎች ያሉበት ማንኛውም መጽሐፍ**

- ይህን ይበሉ, **መጽሐፍት ሥዕሎችና ቃላት አሏቸው።** ወደ አንድ ሥዕል በመጠቆም **ይህ ሥዕሉ ነው** ይበሉ ።  ለቃላትም ይድገሙ።
- ይህን ይበሉ, **አንድ ገጽ ይምረጡ።  ወደ ሥዕሎቹ ይጠቁሙ ።  አሁን ወደ ቃላቱ ይጠቁሙ።**
- ለተጨማሪ ገጾች ይድገሙ።

## አንብብ: ***(Artists Create! )*** *አርቲስቶች ይፍጠሩ!*

**ቁሳቁሶች**: *(Artists Create! ) አርቲስቶች ይፍጠሩ!*

- ከልጁ ጋር ያንብቡ *(Artists Create! ) አርቲስቶች ይፍጠሩ!*
- በኋላ, ስለ ገጽ 20-21 ከልጅዎ ጋር አብረው ይነጋገሩ።  ይጠይቁ ፣ **ምንድነው ሕልም?  ምን ማድረግ ትፈልጋለህ?**




አርቲስቶች ይፍጠሩ!
የተፃፈው በአኪያ ግሮስ    ምስል በብሪይ ዋከር


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።




**መቀሶች**




**ግሉ /ሙጫ**



**ከራሮች**



**እስራስ**



**የኮንስትራክሽን ወረቀት**



**የሥዕል ቡረሽ**



**ኮምፒውተር**



**ካሜራ**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።




መቀሶች




ግሉ /ሙጫ



ከራሮች



እስራስ



የኮንስትራክሽን ወረቀት



የሥዕል ቡረሽ



ኮምፒውተር



ካሜራ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሳምንት 2


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 አጠቃላይ እይታ

## ቀለሞች!



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ ይህንን ያደርጋል:

ስለ ቀለሞች እና ቲንቶች / ትንሽ ቀለሞች የበለጠ ይማራሉ ፣ መደርደርን ይለማመዳሉ እና ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸ( ቃላትን ማግኘት ይለማመዳሉ ።

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



## ኪነ-ጥበብ

ነገሮችን ለመወከል ወይም ሀሳቦችን ለመግለጽ ቀለም ቅብ ፣ ሥዕል ፣ ቅርፃ ቅርፅ ፣ ወዘተ



## ቅርፃ ቅርፅ

በአርቲስት የተሰራ እቃ ፦ ከድንጋይ ፣ ከእንጨት ፣ ከሸክላ ፣ ወይም ከብረት



## ቲንት/ ትንሽ ቀለም

አነስተኛ መጠን ያለው ቀለም


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

አስብበት!

በዚህ ሳምንት የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዓይነቶችን ይሰራሉ። ፓኬቱን ከመጀመርዎ በፊት ስለ እርስዎ ተወዳጅ የኪነ-ጥበብ ዓይነት ይጻፉ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 ቀን 6

## STEM: በጣት መቁጠር

- ልጅዎ በጣቶቹ እንዲቆጥር ያስተምሩት። ይህን ይበሉ፣ **በጣቶቻችን እንቁጠር።** እጃትን ጨብጠው ያሳዩት እና ይህን ይበሉ፣ **ወደላይ የተዘረጉ ጣቶች የሉም ማለት ዜሮ ማለት ነው ።**
  - **1** - ጠቋሚዎን ጣትዎን ያውጡ
  - **2** - ጠቋሚውን እና የመሃል ጣትዎን ያውጡ
  - **3** - ሶስቱን የመሃል ጣቶችዎን ያውጡ
  - **4** - አራት ጣቶችዎን ያውጡ (አውራ ጣት አይደለም)
  - **5** - ሁሉንም ጣቶች ያውጡ እና አውራ ጣትንም
- ይህን ይበሉ, **አሁን ከኔጋ ቁጠር።** በጋራ አንድ ጊዜ ያህል በጣትዎ ይቁጠሩ።
- ይጠይቁ, **1 ጣት ልታሳየኝ ትችላለህ?** የትኛውንም ጣት ቢያሳይዎት ምንም ችግር የለውም ። ለ 2 ጣቶች ይድገሙ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: የቅርፅ ኪነ-ጥበብ

**ቁሳቁሶች: ለልጆች የሚሆን ደህንነቱን የጠበቀ መቀሶች, መፅሔቶች ወይም ጋዜጣ, ወዘተ., ግሉ/ሙጫ ወይም ቴፕ, ወረቀት**


- ይህን ይበሉ, **የተለያዩ ቅርጾችን ቆራርጠው ያውጡ። ከዚያም የቅርጽ ኪነ-ጥበብን ለመስራት በወረቀትዎ ላይ ይለጥፉቸው ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ እንቅስቃሴውን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ። ያልተለመዱ ቅርጾችን ቢቆርጥ፣ ችግር የለውም ፣ መቁረጥን እየተለማመደ ነው!
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **ስለ ኪነ-ጥበብህ ንገረኝ! ምን አይነት ቅርጾችን ተጠቅመሃል?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ



## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ በተዋሃዱ ቃላት ዉስጥ ያሉ ቃላት



**ቁሳቁሶች**: [የተዋሃዱ ቃላት 2]

- ይህን ይበሉ, **አንድ የተዋሃደ ቃል ለመስራት ሁለት ቃላትን በአንድ ላይ ማሰባሰብን እንለማመድ!**
- ለ “strawberries/ ስትሮቤሪስ” ለልጆ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: straw / ስትሮ** (ለአፍታ አቁም) **berries/ ቤሪስ እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው የስትሮቤሪስ ሥዕሉን ያሳዩ) **strawberries / ስትሮቤሪስ!**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **straw / ስትሮ** (ለአፍታ አቁም) **berries/ ቤሪስ ።** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የስትሮቤሪስ ሥዕሉን ያሳዩ ። **strawberries / ስትሮቤሪስ!** ሁለቱን ቃላት ሲያቀናጁ የተዋሃደው ቃል ምን እንደ ሆነ እንዲናገር ልጅዎን ይጠይቁ ። እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም! አሁንም እየተማሩ ነው! ኣብዝተው አድናቆትዋን ይግለፁለት ። **Strawberries! /ስትሮቤሪስ! ታላቅ ስራ!**
- ለነዚህ ቃላቶች ይድገሙ: pancake/ፓንኬክ እና housefly/ ሐውስፉላይ። ሌሎቹን ስዕሎች በዚህ ሳምንት ወደ በኋላ ለሚገኘው እንቅስቃሴ ይሆኑ ዘንድ ያስቀምጧቸው።

## አንብብ: ***Sorting/መደርደር***




**ቁሳቁሶች**: [*Sorting/ መደርደር*]

- ከልጆ ጋር, አንብቡ *Sorting/መደርደር።*
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **ነገሮችን ስንደረድር ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን በአንድ ቡድን ውስጥ እናደርጋቸዋለን ።**
- ይመልከቱ ገፅ. 6-7. ይጠይቁ, **እነዚህ እንዴት ነበር የተደረደሩት?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።





ስትሮ

ቤሪስ



ስትሮቤሪ
ስ





ፓን

ኬክ



ፓንኬክ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።



ቦክስ



ሳንድ



ሳንድቦክስ



ፍላይ



ሃውስ



ሀውስፍላ
ይ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።



ቦይ



ካው



ካውቦይ



ቦክስ



ሹ



ሹቦክስ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 ቀን 7

## STEM: በትናንሽ ቀለሞች /ቲንት ቀለም መቀባት

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ከነጭ ጋር ወይም ከለሮች, ወረቀት**

- ይህን ይበሉ, **በትናንሽ ቀለሞች /ቲንት ቀለም እንቀባ። ከቅመቶች ጋር ቀለም እናድርግ. አንድን ቀለም ከነጭ ጋር ስናቀላቀልጥ ቲንት ወይም ሳሳ ያለ ጥላን እናገኛለን ።**
- ልጅዎ የመረጣቸውን ቀለሞች ከነጭ ጋር ቀላቅሎ ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ዋናዎቹን / ኦርጅናል ቀለሞችን ከቲንቶቹ ጋር ያወዳድሩ። ይጠይቁ, **የትኛው ቀለም የበለጠ ብሩህ ወይም ጠንካራ ይመስላል?**

## እራሱን የቻለ ትምህርት: ቅርፃ ቅርፅ

**ቁሳቁሶች: እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቁሳቁሶች ለምሳሌ ፣ አነስተኛ የካርቶን ሳጥኖች እና ፕላስቲክ ኮንቴይነሮች ፣ ቴፕ ፣ [ቅርፃ ቅርፅ]()**





- ከልጅዎ ጋር የቅርፃ ቅርጾችን ስዕሎች ይመልከቱ ።
- ይህን ይበሉ, **እነዚህን ነገሮች በመጠቀም ቅርፃ ቅርፅ መስራት ትችላለህ ።**
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ቅርፃ ቅርፅ እንዲሠራ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **ዋው, እባክህን በጣም ጠንክረህ ስለሰራኸዉ ቅርፃ ቅርፅ ንገረኝ።**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 ቀን 7

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ገፅ መግለጥ


**ቁሳቁሶች**: **ማንኛውም አይነት መፅሃፍ**

- ከልጅዎ ጋር, መጽሐፍ እንዴት መያዝ እና ገጾቹን መግለጥ እንደሚቻል ይናገሩ ። ይህን ይበሉ, **የፊት ሽፋኑን ማየት እንድንችል መጽሐፉን በፊት በኩል ወደ ላይ እንይዛለን ።** ወደ ፊት ሽፋኑ ይጠቁሙ ። **ከዚያ በኋላ, እያንዳንዱን ገጽ ለማንበብ ገጾቹን በጥንቃቄ እናዞራቸዋለን ።** መፅሃፍ አያያዝን እና ገፆችን ማዞርን በማሳየት እርሶ ምሳሌ ይሁኑ።
- ልጅዎ የፊት እና የኋላ ሽፋኑን እራሱን ችሎ እንዲያሳይዎ እና የመጽሐፉን አንዳንድ ገጾች እንዲያዞሩ ያድርጉት ።

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የአርቲስቶች መሳሪያዎች

**ቁሳቁሶች**: **ከለሮች, የአርቲስቶች መሳሪያዎች የጆርናል ገፅ**

- ከልጆ ጋር, አርቲስቶች ስለሚጠቀሙባቸው የተለያዩ መሳሪያዎች ተነጋገሩ ፣ ለምሳሌ ፣ የፎቶግራፍ አንሺ ካሜራ ወይም የሙዚቀኛ መሣሪያ።
- ልጅዎ ሊሞክረው ስለሚፈልገው የአርቲስት መሣሪያ ዓይነት ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ያንን መሣሪያ ለምን መረጥክ? በመሣሪያው ምን ታደርግበታለህ?**


ስም: ________________

ሊሞክሩት ስለሚፈልጉት የአርቲስት መሣሪያ ይሣሉ እና ይፃፉ ::


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: ________________

ሊሞክሩት ስለሚፈልጉት የአርቲስት መሣሪያ ይሣሉ እና ይፃፉ ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ




## STEM: መደርደር

**ቁሳቁሶች: ማንኪያዎች, ኩባያዎች, ከለሮች, እስራስ (በያንስ ከእያንዳንዱ 2)**

- ይህን ይበሉ, **እነዚህን ነገሮች እንለይ እና ተመሳሳይ የሆኑትን አንድ ላይ እናጣምር ፡፡ ሁሉንም ማንኪያዎች አንድ ላይ አደርጋለሁ ፡፡** ማንኪያዎቹን አንድ ላይ በቡድን በማድረግ ያሳዩ ፡፡
- **ሌሎች የተቀሩትን እንደርድር፡፡** ልጅዋ እቃዎቹን በአንድ ላይ እንዲቦድን ያድርጉት፡፡ ዕቃዎቹን በተለያዩ መንገዶች ለምሳሌ እንደ መጠን ባሉ መንገዶች፣ ቢደረድራቸው ችግር የለውም ፣ እቃዎችን ለመደርደር ብዙ መንገዶች አሉ ፡፡

## እራሱን የቻለ ትምህርት: የቀለም ተሽከርካሪ ኮላጅ

**ቁሳቁሶች: [ቀለም የሌለው ተሽከርካሪ, የቀለም ተሽከርካሪ] ከ ሳምንት 1, ለልጆች የሚሆን ደህንነቱን የጠበቀ መቀሶች, ግሉ, መፅሔት ወይንም በራሪ ወረቀት ወይም ከለር እስራስ ወይም ከለሮች.**




- በቀለም ተሽከርካሪ ውስጥ ያሉትን ቀለሞች ይሰይሙ ፡፡
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ስዕሎች በቀለም ተሽከርካሪው ላይ ማጣበቅ ይችላሉ፡፡** አንድ በጋራ ይስሩ፡፡ ስዕል ፈልገው ይቁረጡ እና በሚዛመደው ቀለም ላይ ይጣብቁት ፡፡
- ልጅዎ ራሱን ችሎ እንቅስቃሴውን እንዲሠራ ያድርጉ፡፡ ስዕሎችን ካላገኘ በምትኩ በቦታው /በስፔሱ ውስጥ አንድ ነገር መሳል ይችላል፡፡
- በኋላ, ስለ ቀለሞች እና ስዕሎች አንድ ላይ ይነጋገሩ፡፡


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ




## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ስለ ሁኔታው ንገረኝ

- ይጠይቁ, **ስለ ቀለሞች እና ኪነ-ጥበባት እየተማርን ነበር ። እስካሁን ድረስ የእርስዎ ተወዳጅ ክፍል ምንድነው?**
- ልጅዎን 2-3 የሚሆኑ የመከታተያ ጥያቄዎችን ይጠይቁ እንደ, **ለምን ይመስልሃል?** ወይንም, **ሌላ ምን መማር ትፈልጋለህ?** መልስ በመመላለስ ውይይት ማድረግን ተለማመዱ ።
ስለ ቀለም እና ስለ ኪነ - ጥበብ ማውራት የማይፈልግ ከሆነ ልጅዎን በምትኩ ስለ ምን ማውራት እንደሚፈልግ መጠየቅ ይችላሉ።

## አንብብ: ***(Sorting)*** *መደርደር*

**ቁሳቁሶች**: *(Sorting) መደርደር*, **ሊደረደሩ የሚችሉ የቤት ቁሳቁሶች ፣ ለምሳሌ ፣ ማንኪያዎች እና ኩባያዎች ወይም ቀይ እና ቢጫ መጫወቻዎች**




- ከልጆ ጋር, አንብቡ *Sorting / መደርደር*
- በኋላ, ይጠይቁ, **አሁን መደርደርን እንለማመድ። እነዚህን መደርደር ትችላለህ?** ያስታውሱ ፣ ልጅዎ አሁንም ለመደርደር የተለያዩ መንገዶች ሊኖሩት ይችላል ፤ያም ትክክለኛ መንገድ ነው። የተወሰኑ ነገሮችን በአንድ ላይ ለምን እንደሰበሰ ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ሳምንት 4 ሳምንት 2 ቀን 8

## እንቀሳቀስ፡ ቁጠር እና ደንስ

**ቁሳቁሶች**: ***አማራጭ - ሙዚቃ***


- ይህን ይበሉ, **እየደነስን እስከ 5 ድረስ እንቁጠር ።**
- እርሶም እስከ 5 እየቆጠሩ እንዲደንሱ፣ ልጅዎ የተለያዩ የዳንስ እንቅስቃሴዎችን እንዲጠቁም ይፍቀዱለ።

## በጋራ መማር፡ ከሙዚቃው ጋር ቀለም መቀባት

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች, ወረቀት, የተለያዩ የሙዚቃ አይነቶች**

- ይህን ይበሉ, **የተለያዩ አይነት ሙዚቃዎችን እናዳምጣለን ። እያዳመጥን እያለ የሚሰማንን ቀለም እንቀባለን ።**
- 2-3 የተለያዩ የሙዚቃ አይነቶችን ያጫውቱ ፣ ለምሳሌ ፈጠን ያለ እና ቀስ ያለ ምት ያለው ሙዚቃ። በአንድ ወረቀት ላይ በጋራ መቀባት ወይም በተለያዩ ወረቀቶች ላይ ለየብቻ መቀባት ይችላሉ ።
- በኋላ, የተለያዩ ሙዚቃዎች እርስዎን ወይንም ልጅዎን ምን አይነት ስሜቶች እንዲሰማችሁ እንዳደረጉ እናም ቀለም ቅባችሁ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ እንዳደረሱ አወዳድሩ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 ቀን 9

## **STEM: Tessellations /**ተሰሌሽንስ ቀለም መቀባት

**ቁሳቁሶች**: **ተሰሌሽን, ከለሮች, *አማራጭ - ግሉ እና ወረቀት***



- ይህን ይበሉ, **ተሰሌሽን ማለት የቅርፃ ቅርፆች ፓተርን /ድግግሞሽ ነው, ቅርፃ ቅርፆችን ደጋግመን ስንጠቀም እንደ ፓተርን። እንዴት ያለ ረጅም ቃል ነው! ይህንን ተሰሌሽን ቀለም መቀባት ትችላለህ።**
- ልጁ እራሱን ችሎ የራሱን ተሰሌሽን ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ።
- በኋላ, ስለ ዲዛይናቸው እና ስለተጠቀሙባቸው ቀለሞች ተነጋገሩ ።
- *አማራጭ - የተለየ ተሰሌሽን ለመሥራት ቀለሙን ከቀቡ በኋላ ስዕሉን ቆርጠው ቁርጥራጮቹን በሌላ ወረቀት ላይ ይለጥፉ።*

## እራሱን የቻለ ትምህርት : የነጥብ ኪነ –ጥበብ

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት, ወረቀት, የቀለም መቀበያ ብሩሽ, ያልሾላ እስራስ ወይም የጥጥ ቁርጥራጭ**

- ይህን ይበሉ, **ነጥቦችን በመጠቀም ኪነ-ጥበብን መፍጠር ትችላለህ።** ነጥቦችን ለመሥራት ፣የቀለም ብሩሹን ፣ የእርሳሱን ወይም የጥጥዎቹን የታችኛውን ጫፍ እንዴት ቀለም ውስጥ እንደሚነክሩ እና ከዚያም ወደ ወረቀቱ ላይ እንደሚያሰፍሩ ለልጅዎ ያሳዩ ። ልጅዎ እራሱን ችሎ የዶት ጥበብን እንዲሠራ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, እባክህን **ስለ ኪነ-ጥበብህ ንገረኝ ። ምን ዓይነት ቀለሞች ተጠቅመሃል?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 ቀን 9

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: **Hey Diddle Diddle /ሄ ዲድል ዲድል**

ሄይ ዲድል ዲድል



ሄይ ዲድል ዲድል
ዘ ካት ኤንድ ዘ ፊድል,
ዘ ካው ጃምፕድ ኦቨር ዘ ሙን;
ዘ ሊትል ዶግ ላፍድ
ቱ ሲ ሰች ስፖርት,
ኤንድ ዘ ዲሽ ራን
አዌይ ዊዝ ዘ
ስፑን

**ቁሳቁሶች**: Hey Diddle Diddle /ሄ ዲድል ዲድል

- ተመሳሳይ የድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላት ማዳመጥን ተለማመድ። ይህን ይበሉ, **ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች የመጨረሻዎቹ ፊደሎቻቸው ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ አላቸው፣ እንደ hut /ሐአት እና cut/ከአት። አንድ ግጥም እናንብብ እና ተመሣሣይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላቶች /ራይሚንግ ወርድስ እናዳምጥ ።**
- በጋራ, ግጥም አንብቡ። ይህን ይበሉ፣ **መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው አንዳንድ ቃላቶች ስምቻለው። Diddle/ዲድል እና fiddle/ፊድል**
- ግጥሙን ቀስ ብለው እንደገና ያንብቡ። ይጠይቁ, **ምን አይነት ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች ሰምተሃል?** (diddle/ዲድል-fiddle/ፊድል, moon/ሙን, spoon /ስፑን)። ልጅዎ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ቃላትን ለመለየት የሚቸግረው ከሆነ ፣ ችግር የለውም። አሁንም እየተማረ ነው! ቃላቱን ለይለት።

## የፅሁፍ ሃሳብ: የሙዚቃ መሳሪያዎች

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የሙዚቃ መሳሪያዎች የጆርናል ገፅ**


- ከልጅዎ ጋር ስለ የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች አይነቶች ይናገሩ።
- ልጅዎ ሊሞክረው ስለሚፈልገው የሙዚቃ መሣሪያ ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ይህንን መሣሪያ ለምን መረጥከዉ? በመሳሪያው ምን ዓይነት ሙዚቃ መጫወት ትፈልጋለህ?**




ስም: ________________

ሊሞክሩት ስለሚፈልጉት የሙዚቃ መሣሪያ ይሳሉ እና ይፃፉ፡፡


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: ________________

ሊሞክሩት ስለሚፈልጉት የሙዚቃ መሣሪያ ይሳሉ እና ይፃፉ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 ቀን 10

## **STEM:** መደርደር ሁለት

**ቁሳቁሶች: ማንኪያዎች ፣ ኩባያዎች ፣ ከለሮች, እርሳሶች (እያንዳንዳቸው ቢያንስ 2)**

- ይህን ይበሉ, **ባለፈዉ ጊዜ እነዚህን ዕቃዎች ከለየን በኋላ ተመሳሳይ ነገሮችን አንድ ላይ አድገናል ። እነዚኑ ለመደርደር የምንችልበትን ሌላ መንገድ ማሰብ ትችላለህን?**
- **በአጠቃቀማቸው ልንለያቸው እንችላለን ። ለመፃፍ የምንጠቀምባቸውን ነገሮች** (ከለሮች ፣ እርሳሶች) **በአንድ ቡድን ውስጥ እና ለመብላት እና ለመጠጣት የምንጠቀምባቸውን ነገሮች** (ኩባያ ፣ ማንኪያ) **በሌላ ውስጥ እናድርጋቸው ።**
- ነገሮችን ለመደርደር ብዙ መንገዶች አሉ ። ልጅዎ እነዚኑ ለመደርደር ሌላ መንገድ ሊጠቀም ይችላል (ለምሳሌ በቀለም ፣ በመጠን ፣ ቅርፅ ወዘተ) ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: **Rock Garden /**ሮክ ጋርደን

**ቁሳቁሶች: ጨው ወይም ቆሻሻ ፣ ጠጠሮች ወይም በራሪ ወረቀቶች ፣ ሹካ ፣ ሳህን ወይም ትሪ ፣** Rock Garden /ሮክ ጋርደን

- ይህን ይበሉ, **በድንጋዮች ኪነ-ጥበብን መስራት ይችላሉ!** rock garden/ ሮክ ጋርደን ሥዕሎችን ይመልከቱ ።
- ጠጠሮችን ጨው በያዘው ሳህን /ትሪ ላይ በማስቀመጥ በራክ /መደልደያ ሹካው በማስተካከል፤ ልጅዎ ራሱን ችሎ የ rock garden/ ሮክ ጋርደን ቦታቸውን እንዲነድፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **እባክህን ስለ rock garden/ ሮክ ጋርደን ስፍራህ ዲዛይን ንገረኝ ። ለምን በዚያ መንገድ ሰራኸው?**







©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 2 ቀን 10

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የተዋሃዱ ቃላቶች


**ቁሳቁሶች**: **[የተዋሃዱ ቃላቶች 2]** **በዚህ ሳምንት ከዚህ በፊት**



- ይህን ይበሉ, **አንድ የተዋሃደ ቃል ለመስራት ሁለት ቃላትን በአንድ ላይ ማሰባሰብን እንለማመድ!**
- ለ "sandbox/ ሳንድቦክስ" ለልጆ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: sand / ሳንድ** (ለአፍታ አቁም) **box/ ቦክስ ። እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው የሳንድቦክስ ሥዕሉን ያሳዩ) **sandbox / ሳንድቦክስ!**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **sand / ሳንድ** (ለአፍታ አቁም) **box/ ቦክስ ።** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የሳንድቦክስ ሥዕሉን ያሳዩ ። **sandbox / ሳንድቦክስ! ታላቅ ስራ!**
- ለነዚህ ቃላቶች ይድገሙ: shoebox/ ሹቦክስ እና cowboy/ ካውቦይ። 2ቱ ቃላት ሲያቀናጁ የተዋሃደው ቃል ምን እንደ ሆነ እንዲናገር ልጅዎን ይጠይቁ ። እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም! አሁንም እየተማረ ነው! አብዝተው አድናቆትዎን ይግለፁለት ።

## አንብብ: ***(Sorting) መደርደር***

**ቁሳቁሶች**: *[(Sorting) መደርደር]*




- ከልጆ ጋር, አንብቡ (*Sorting*) *መደርደር*
- በኋላ, ለልጆ ያሳዩት ገፅ.18-19. ይጠይቁ, **እነዚህን ነገሮች እንዴት መደርደር እንችላለን?** የምንደረድረው በቀለም ፣ በዕፅዋት እና በእንስሳት ፣ በሚበሉ ነገሮች እና በማይበሉ ነገሮች ሊሆን ይችላል።
- ልጅዎ እንዲሁ በሌላ መንገድ ለመደርድር ያስብ ይሆናል ፣ ያም ልክ ነዉ!


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።


# ሳምንት 3



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# PK3 ክፍል 4 ሳምንት 3 አጠቃላይ እይታ

## በዙሪያችን ሁሉ ያሉ ቀለሞች



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ ይህንን ያደርጋል:

የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዓይነቶችን መመርመሩን ይቀጥላል ፣ ስለ ቀስተ ደመናዎች ይማራል እና እቅድ ያወጣና ድግስ/ ፖርቲ ያዘጋጃል! መጠኖቻቸውን ያነፃፅራ ል እና የተዋሃዱ ቃላትንም ያዘጋጃል።

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



**ኪነ -ጥበብ**

ነገሮችን ለመወከል ወይም ሀሳቦችን ለመግለጽ ቀለም ቅብ ፣ ሥዕል ፣ ቅርፃ ቅርፅ ፣ ወዘተ



**ቀስተ ደመና**

በሰማያት ውስጥ አንድ ትልቅ የቀለሞች ከርቭ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

አስብበት!

በዚህ ሳምንት, የሚወዱትን የቀለም መጽሐፍዎን ያዘጋጃሉ። ፓኬቱን ከመጀመርዎ በፊት በሚወዷቸው ቀለሞች ስዕል ይሳሉ!


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ



## STEM: ትልቅ, ትንሽ

**ቁሳቁሶች: ያየ መጠን ያላቸውን ብሎኮች ወይም የወረቀት ፎጣ/ በተለያዩ መጠኖች የተቆራረጡ የመጸዳጃ ወረቀት ጥቅልሎች**

- ከልጃ ጋር, የተለያዩ መጠን ያላቸውን ብሎኮች ማወዳደር። ይጠይቁ, **የትኛው ብሎክ ትልቅ ነው? እንዴት አወቅኽ?** እና, **ትንሹን ብሎክ ስጠኝ, እባክህን።**
- ሁለት ብሎኮችን ያሳዩ እና  ከትንሽ እስከ ትልቁ ብሎክ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጣቸው ልጅዎን ይጠይቁ። በኋላ, ይጠይቁ, **የትኛው ብሎክ ይተልቃል?  የትኛው ያንሳል?**
- ከዚያ, ልጅዎ 2 የተለያዩ ብሎኮችን እንዲመርጥ እና እንዲያነፃፅር ይጠይቁ። ይጠይቁ, **ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ናቸው ወይስ አንዱ ትልቅ ነው?**  ለሌላ ጥንድ ብሎኮች ይድገሙ ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: በብዙ ከለሮች ቀለም መቀባት

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, ወረቀት, የገንዘብ ላስቲክ ወይም ገመድ**


- ይህን ይበሉ, **በአንድ ጊዜ በበርካታ ከለሮች ቀለም ቀባ እና ምን እንደሚከሰት ማየት ትችላለህ ።**
- ልጅዎ በበርካታ ከለሮች ዙሪያ የገንዘብ ላስቲኩን እንዲጠመጥም /እንዲያደርግ ይርዱት ።
- እስሩን /ጥቅሉን በመጠቀም ልጅዎ ራሱን ችሎ ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **በተመሳሳይ ጊዜ በብዙ ከለሮች ተጠቅሞ ቀለም መቀባት ምን ይመስላል?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ

PK3 **ክፍል** 4 **ሳምንት** 3 **ቀን** 11

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: የተዋሃዱ ቃላቶችን መመስረት



**ቁሳቁሶች**: **[የተዋሃዱ ቃላቶች 3]**

- ይህን ይበሉ, **አንድ የተዋሃደ ቃል ለመስራት ሁለት ቃላትን በአንድ ላይ ማሰባሰብን እንለማመድ!**
- ለ “doorbell/ ዶርቤል” ለልጆ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: door / ዶር** (ለአፍታ አቁም) **bell/ ቤል ። እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው የዶርቤል ሥዕሉን ያሳዩ) **doorbell / ዶርቤል!**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **door / ዶር** (ለአፍታ አቁም) **bell/ ቤል ።** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የዶርቤል ሥዕሉን ያሳዩ ። **doorbell / ዶርቤል! ታላቅ ስራ!**
- ለነዚህ ቃላቶች ይድገሙ: firefly/ **ፋየር ፍላይ** እና sunflower/ ሰን ፍላወር። ልጅዎ 2ቱ ቃላቶች የፈጠሩትን የተቀናጀ ቃል እንዲነግርዎ እንዲሞክር ያድርጉ ። እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም! አሁንም እየተማረ ነው!
- ሌሎቹን ስዕሎች በዚህ ሳምንት ወደ በኋላ ለሚገኘው እንቅስቃሴ ይሆኑ ዘንድ ያስቀምጧቸው።

## አንብብ: ***(Party Plans )*** *የፓርቲ ዕቅዶች*




**ቁሳቁሶች**: ***[(Party Plans) የፓርቲ ዕቅዶች]***

- ከልጆ ጋር, አንብቡ (*Party Plans*) *የፓርቲ ዕቅዶች።*
- በኋላ, ስለ ጀርሞች ጠንቃቃ ስንሆን ወይም ቤተሰቦቻችን እና ጓደኞቻችን ርቀው በሚኖሩበት ጊዜ ፓርቲዎች እንዴት እንደሚለያዩ ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ ።
- በአንድ ፓርቲ ውስጥ በትልቅ ቡድን ውስጥ ደህንነታቸውን መጠበቅ የሚችሉባቸውን መንገዶች እንዲያስቡ ይጠይቋቸው ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።



ፍላይ



ፋየር



ፋየርፍላይ



ቤል



ዶር



ዶርቤል


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።



ሰን



ፍላወር



ሰንፍላወር



ሬን



ኮት



ሬንኮት


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።



ኢር



ሪንግ



ኢርሪንግ



ሄር



ብረሽ



ሄርብረሽ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ማክሰኞ



## STEM: ቀስተ ደመና

**ቁሳቁሶች**: [**ባዶ ቀስተ ደመና**](), [**ቀስተ ደመና**](), **ከለሮች**



- የቀስተ ደመና ስዕሎችን አሳይ። ይህን ይበሉ, **ቀስተ ደመና የሚፈጠረው የፀሐይ ብርሃን በዝናብ ጠብታዎች ውስጥ ሲያልፍ ነው። ስለዚህ ትክክለኛውን ነጭ ቀለም የሠሩትን ሁሉንም ቀለማት ማየት እንችላለን ማለት ነው።**
- **ቀለሞች ሁል ጊዜ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ተደርድረው ይገኛሉ - ROYGBIV – red/ ቀይ, orange / ብርቱካናማ, yellow/ቢጫ, green/ አረንጓዴ, blue/ሰማያዊ, indigo /ኢንዲጎ, violet / ቫዮሌት።**
- **አሁን በራስህ ቀስተ ደመና ውስጥ ቀለም ትቀባለህ።** ልጅዎ በቀስተደመናው ውስጥ ራሱን ችሎ ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ። ቀለሞችን በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ሳያስቀምጥ ቢቀር፣ ችግር የለውም ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: ፓርቲን ማቀድ

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች, ወረቀት**

- ይህን ይበሉ, **ነገ የራሳችን የሆነ ትንሽ ድግስ/ፓርቲ እናካሂዳለን እናም አሁን ማቀድ ትችላለህ ።**በቤት ውስጥ ግብዣ/ ፓርቲ ለማድረግ ቀላል መንገዶችን በአዕምሮአቸው እንዲያፈልቅ ይርዱት ።
- ልጅዎ እነሱን ችሎ ፓርቲውን ለማድረግ ያስቀመጠውን ዕቅድ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ነገ ምን አይነት ድግስ/ፓርቲ እናደርጋለን? እስቲ ስለዚህ ጉዳይ ንገረኝ ።**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 3 ቀን 12

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቀለሞች

**ቁሳቁሶች**: [የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቀለሞች]

- ተመሳሳይ የድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላት ማዳመጥን ተለማመድ። ይህን ይበሉ, **ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች የመጨረሻዎቹ ፊደሎቻቸው ተመሳሳይ የድምፅ አወጣጥ አላቸው፣ እንደ snap /ስናፕ እና clap/ክላፕ። አንድ ግጥም እናንብብ እና ተመሣሣይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላቶች /ራይሚንግ ወርድስ እናዳምጥ ።**
- **በጋራ**, ግጥም አንብቡ። ይህን ይበሉ፣ **መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው አንዳንድ ቃላቶች ስምቻለው። Blue/ብሉ እና do/ዱ**
- ግጥሙን ቀስ ብለው እንደገና ያንብቡ። ይጠይቁ, **ምን አይነት ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች ሰምተሃል?** (blue/ብሉ -do/ዱ, see/ሲ-be/ቢ, green/ግሪን -scene/ሲን)። ልጅዎ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ቃላትን ለመለየት የሚቸግረው ከሆነ ፣ ችግር የለውም። አሁንም እየተማረ ነው! ቃላቱን ለይለት።


የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቀለሞች


ካትሪን አሱሊቫን

ሬድ, የሎ, ብሉ.
ዋት ካን ዜ ዱ? ዚስ ፕላይመሪ ከለርስ
ካን ቢ ሚክስድ ቱጌዘር, ዩ ሲ.
ዜይ ሜክ ሰከንደሪ ከለርስ.
ዋት ማይት ዜይ ቢ?
ፐርፐል, ኮሬንጅ, ግሪን.
ፑት ዘም አል ቱጌዘር.

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የኔ ፓርቲ


**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የኔ ፓርቲ ጆርናል ገፅ**

- ከልጅዎ ጋር ነገ ስላቀደው ፖርቲ ተነጋገሩ።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ የግብዣ /ፓርቲ መጥሪያ ለእርስዎ ወይም ለሌላ ሰው (በአካል ወይም በምናባዊ /ቨርቹአል ሊመጣ ለሚችል) አዘጋጅቶ እንዲሰጥ ያድርጉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **እባክህን ስለ ግብዣህ ንገረኝ ።**


ስም: ________________

ሊደግሱ ስለሚፈልጉት ፓርቲ ወይንም አወደ ርእይ /ትሪት የግብዣ መጥሪያ ያዘጋጁ።

PK3 ኪነ-ጥበብ እና ቀለም
©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።








©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ቀለሞች

ካትሪን
ኦሱሊቫን



ሬድ, የሎ, ብሉ.
ዋት ካን ዜ ዱ? ዚስ ፕላይመሪ
ከለርስ ካን ቢ ሚክስድ ቱጌዘር, ዩ
ሲ.
ዜይ ሜክ ሰከንደሪ ከለርስ.
ዋት ማይት ዜይ ቢ?
ፐርፕል, ኦሬንጅ, ግሪን.
ፑት ዘም ኦል ቱጌዘር.


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: _________________

ሊደግሱ ስለሚፈልጉት ፓርቲ ወይንም አወደ ርእይ /ትሪት  የግብዣ መጥሪያ ያዘጋጁ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 3 ቀን 13

## STEM: ሲሜትሪ

**ቁሳቁሶች: ግማሽ ላይ የታጠፈ ወረቀት, የውሃ ቀለም ፖሌት**

- ይህን ይበሉ, **ሲሜትሪን የሆነ ስዕል ትስላላህ ። ሲሜትሪ ማለት በሁለቱም በኩል በትክክል የሚመሳሰል ማለት ነው ።**
- ከታጠፈው ወረቀት ላይ ወደ አንዱ ግማሽ ያመልክቱ። ይህን ይበሉ, **መጀመሪያ የወረቀቱን አንድ ጎን ብቻ ይሳሉ ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ሌላኛውን ጐን ቀለም እንዲቀባ ያድርጉት ።
- በኋላ, ልጅዎ ወረቀቱን እንዲያጥፍ እና ሁለቱን ግማሾችን በአንድ ላይ እንዲጫናቸው ይርዱት ።ከዚያ ወረቀቱን ይክፈቱ እና ሁለቱን ግማሾች ከልጅዎ ጋር ያወዳድሩ። በሁለቱም በኩል ተመሳሳይ ቅርፅ ያላቸው አንዱ የሌላው የመስታወት ምስል /ግልባጭ መምሰል አለበት ። ይጠይቁ, **ስለ እያንዳንዱ ጐን ምን አስተዋልክ?**

## እራሱን የቻለ ትምህርት: የውሃ ቀለም እና Crayon ሪሊፍ

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ከለሮች, የውሃ ቀለም ፖሌት**

- ይህን ይበሉ, **ኪነ-ጥበብን ለመሥራት ከለሮች እና ቀለምን ሊጠቀሙ ነው።**
- **በመጀመሪያ ፣ የሚፈልጉትን ነገር በከለሮች ይሳሉ ። ከዚያ ፣ በስዕልዎ ላይ ቀለም ይቀቡ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ እንዲስል እና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **በወረቀቱ ላይ ብቻ ቀለም ሲቀቡ ምን ይከሰታል? በከለሮች ስዕሉ ላይ ቀለም ሲቀቡ ምን ይከሰታል?** ቀለም ቅቡ የcrayon ቀለም ባላቸው አካባቢዎች ላይ አይጣበቅም /አይዝም፣ በሰሙ ምክንያት። **ለምን እንዲህ የሆነ ይመስልሃል?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 3 ቀን 13

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: አንድን ገፅ ማብራራት


**ቁሳቁሶች**: Party Plans



- ልጅዎን ገጽ 4-5 ያሳዩ። ይህን ይበሉ ፣ **በዚህ ገጽ ላይ ያሉትን ስዕሎች ተመልከት ። እየሆነ ነው ብለህ የምታስበውን ነገር ንገረኝ።** ያስታውሱ ፣ ልጅዎ ገጹን በተለየ መንገድ ሊተረጉመው ይችላል እና ያ ችግር የለውም።
- ይጠይቁ, **ምን አይነት ስሜት እየተሰማቸው ነው ብለው ታስባለህ? እንዴት ማወቅ ትችላለህ?**

## አንብብ: (***Party Plans*** ) *የፓርቲ ዕቅዶች*

**ቁሳቁሶች**: *(Party Plans) የፓርቲ ዕቅዶች*



- ከልጅዎ ጋር, ያንብቡ (*Party Plans*) *የፓርቲ ዕቅዶች*
- በኋላ, ስለ ገጽ 8-9 ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ። ይጠይቁ, **ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው? አዎ ተራ በተራ እየተቀያየሩ ነው። በቡድን ውስጥ ስንጫወት ሌላ ምን ማድረግ አለብን?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 3 ቀን 13

## እንቀሳቀስ፡ ትልቁ, ረዥሙ, አጭሩ

**ቁሳቁሶች**: ***አማራጭ - ሙዚቃ***

- ይህን ይበሉ, **እራሳችንን ትልቁ ፣ ትንሹ ፣ ረዥሙ ወይም አጭሩ ለማድረግ የተለያዩ እርምጃዎችን የምንወስድበት ጨዋታ እንጫወት ።**
- የተለያዩ ትዕዛዞችን ያስተላልፉ /ይዘዙ ፣ **ረዥም እንሁን** እና እንዴት በእግር ጣቶች ላይ በመቆም ወይም እጆችዎን ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ሞዴል ይሁኑ /ምሳሌ ይስጡ ፣ ወይም **ትንሽ እንሁን** እና ራስዎን እንደ ኳስ ይጠፉ ።
- ልጅዎ መመሪያ እንዲሰጥዎ ሚናዎችን ተቀያየሩ።

## በጋራ መማር፡ የኛ ፓርቲ

**ቁሳቁሶች: ልጅዎ ለፓርቲው የመረጠው የቤት ቁሳቁሶች፣ የጆርናል / የመፅሔት ገጽ እና የከዚ በፊቱ የፓርቲ ግብዣ መጥሪያ**

- ይህን ይበሉ, **ትናንት አንተ ፓርቲ አዘጋጅተህልናል/አቅደህልን ነበር ፤አሁን ደግሞ ፓርቲያችንን በጋራ እናካሂዳለን!** ስለ ፓርቲ እቅዱ በጋራ ተነጋገሩ እና ፓርቲውን እንዲያቋቁሙ ይርዱት ፣ ለምሳሌ. ቀለል ያለ የፍራፍሬ ዲዘርት ማዘጋጀት እና ቀለል ያሉ ማስጌጫዎችን መጨመር።
- በፓርቲው ላይ ይዝናኑ!


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 3 ቀን 14

## STEM: ፎቶዎችን ማንሳት

**ቁሳቁሶች: ስልክ, ታብሌት, ወይም ዲጂታል ካሜራ**

- ይህን ይበሉ, **ፎቶግራፍ አንሺዎችም አርቲስቶች ናቸው። በጣም አሪፍ ፎቶግራፎችን ለማንሳት ትክክለኛውን ብርሃን መጠቀም ያስፈልጋቸዋል ፣ ስለሆነም በትክክል ማየት እንችላለን። እስቲ የተወሰኑ ምስሎችን እናንሳ እና በብርሃን ሙከራ እናድርግ።**
- ከልጅዎ ጋር ፣የአንድ ተመሳሳይ ክፍልን ወይም እቃን የተለያዩ ምስሎችን ፍላሽ አብርተው እና ከዚያ አጥፍተው ፣ በክፍሉ ዉስጥ ያለዉን መብራቱን አብተዉ እና አጥፍተው ፣ የመስኮቱን መጋረጃዎች ከፍተው ወይም ዘግተው ፣ ወይም እንደ ቁምሳጥን ክፍል ያለ ጨለማ ላይ ሄደው ፎቶ ያንሱ ።
- ስዕሎቹ ብርሃኑን መሠረት አድርገው ምን እንደሚመስሉ ያነፃፅሩ ። ይጠይቁ, **የትኛው ሥዕል በጣም ጥሩ ነው? ይህ ክፍል / ነገር ምን ዓይነት መብራት ነበረው?**
- የካሜራ ማግኘት ካልቻሉ፣ አንድ ነገርን በብርሃናማ ክፍል ውስጥ እና ከዚያ በጨለማ ክፍል ውስጥ ወይም ቁም ሣጥን ውስጥ ያስቀምጡ። እቃውን ማየት ቀላል ወይም ከባድ ስለነበረበት ሥፍራ ይናገሩ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: ተወዳጅ የቀለም መጽሐፍ ክፍል 1

***ቁሳቁሶች: ጥቂት የወረቀት ሉኮች ፣ የውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች, አማራጭ - ግሉ, ደህንነቱን የጠበቀ የልጆች መቀሶች, መፅሔት ወይም ጋዜጣዎች***

- ስለሚወዷቸው ቀለሞች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ። ይህን ይበሉ, **የምትወዳቸውን ቀለሞች የያዘ መጽሐፍ ማዘጋጀት ትችላለህ ። እያንዳንዱን ገጽ ላይ የተለየ ቀለም እንጠቀም ። የምትወደውን ቀለም የያዙ ምስሎችን በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማጣበቅ ትችላለህ ወይንም በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የራስህን ስዕሎችን መቀባት ትችላለህ ።**
- ለእያንዳንዱ ቀለም በተለያዩ ገጾች ላይ ልጅዎ ራሱን ችሎ ሥዕሎችን እንዲስል እና / ወይም እንዲለጠፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, የቀለሙን ቃላት እንዲጽፍ ይርዱት እና ይጠይቁ, **በመጽሐፍህ ውስጥ የትኞቹን ቀለሞች ለማስቀመጥ ወስነሃል?**
- ይህን ይበሉ, **ነገ ሽፋኑን ሠርተው መጽሐፉን በአንድ ላይ ያጣምራሉ ።** ለነገ እንቅስቃሴ መጽሐፉን ያስቀምጡ ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ



## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የእኔ እርምጃዎችን ይግለጹ

- ይህን ይበሉ, **ጨዋታ እንጫወት። አንድ ነገር ላደርግ ነው። አንተ እያደረግሁ ያለሁትን ትገልፃለህ ወይም ትነግረኛለህ።**
- ልጅዎ ሊገልፃቸው የሚችላቸውን ቀላል ድርጊቶች ያድርጉ ፣ለመዘመር ፣ ለመቀባት ፣ ለመደነስ ፣ ፎቶግራፍ ለማንሳት ፣ ወዘተ. በማስመሰል።
- ሚናዎችን ይቀይሩ ልጅዎ እርስዎ እንዲገልጹለት አንድ እርምጃ እንዲወስድ ያድርጉ።

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የቡድን እንቅስቃሴ

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የቡድን እንቅስቃሴ ጆርናል ገፅ**

- ከልጅዎ ጋር፣ ልጅዎ በቡድን ማድረግ ስለሚወዳቸው ነገሮች ለምሳሌ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ መዘመር ወይም ከቤተሰብ አባላት ጋር መጫወት።
- ልጅዎ፣ በቡድን ውስጥ ማድረግ ስለሚወደው ነገር እነሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **በቡድን ምን ማድረግ ትወዳለህ? ለምን ወደድከው?**


ስም: ________________

በቡድን ማድረግ ስለሚወዱት ነገር ይሳሉ እና ይፃፉ ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: ________________

በቡድን ማድረግ ስለሚወዱት ነገር ይሳሉ እና ይፃፉ ፡፡



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 3 ቀን 15

## STEM: ረጅሙ የትኛው ነው?

**ቁሳቁሶች: የተለያየ ርዝመት ያላቸው የቤት ቁሳቁሶች ፣ ለምሳሌ እርሳሶች ፣ ኮንቴይነሮች**

- ይህን ይበሉ, **ርዝመትን ወይም አንድ ነገር ምን ያህል ርዝመት እንዳለው እናነፃፅር ።** የተለያየ ርዝመት ያላቸውን ሁለት ነገሮችን ወደታች አስቀምጥ ። ይጠይቁ, **የትኛው ይረዝማል?** ለልጁ መልሱን መንገር ካለብዎት ችግር የለውም ።
- ለ 2-3 ተጨማሪ ጥንድ ስብስቦችን ይድገሙ። እንዲሁም የትኛው አጭር እንደሆነ እንዲያሳዩ መጠየቅ ይችላሉ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት: ተወዳጅ የቀለም መጽሐፍ ክፍል 2

**ቁሳቁሶች: በተወዳጅ የቀለም መጽሐፍ ክፍል 1 ጊዜ የተሰሩ ገጾች ፣ከለሮች ወይም የውሃ ቀለም ቤተ-ስዕል ፣ ስቴፕለር ወይም ክር እና ቀዳዳዎችን ለመስራት አንድ ነገር**

- ይህን ይበሉ, **ትናንት ለሰራኸውን የቀለም መጽሐፍ ሽፋኑን መስራት እና ማስዋብ ትችላለህ ። ስምህን መጻፍህን እንዳትዘነጋ ።** ልጅዎ ስሙን በሽፋኑ ላይ እንዲጽፍ ይርዱት ።
 ልጅዎ ራሱን ችሎ ሽፋኑን እንዲሠራ ያድርጉ ።
- በኋላ, መፅሃፉን በአንድ ላይ ለማያያዝ በስቴፕለር መምታት ወይንም ቀዳዶችን በመብሳት (አዋቂዎች ብቻ ) እና በክር ቀዳዶቹን በመስፋት ልጁን ይርዱት ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ

PK3 ክፍል 4 ሣምንት 3 ቀን 15

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: የተዋሃዱ ቃላትን እንመስርት

**ቁሳቁሶች**: **[የተዋሃዱ ቃላት 3]** **በዚህ ሳምንት ከዚህ በፊት**



- ይህን ይበሉ, **አንድ የተዋሃደ ቃል ለመስራት ሁለት ቃላትን በአንድ ላይ ማሰባሰብን እንለማመድ!**
- ለ “raincoat/ ሬንኮት” ለልጆ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: rain /ሬን** (ለአፍታ አቁም) **coat/ ኮት። እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው የሬንኮት ሥዕሉን ያሳዩ) **raincoat / ሬንኮት።**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **rain /ሬን** (ለአፍታ አቁም) **coat/ ኮት ።** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የሬንኮት ሥዕሉን ያሳዩ ። **raincoat / ሬንኮት!**
- ለነዚህ ቃላቶች ይድገሙ: earring/ኢርሪንግ እና hairbrush/ ሄርብረሽ ። ልጅዎ 2ቱ ቃላቶች የፈጠሩትን የተቀናጀ ቃል እንዲነግርዎ እንዲሞክር ያድርጉ ። እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም! አሁንም እየተማረ ነው!

## ጮክ ብሎ ማንበብ: ***(Party Plans)*** የፓርቲ እቅዶች

**ቁሳቁሶች**: *[(Party Plans) የፓርቲ እቅዶች]*




- ከልጅዎ ጋር, ያንብቡ(*Party Plans* ) *የፓርቲ እቅዶች።*
- በኋላ, ከልጅዎ ጋር ስለ ገፅ.12-13 ያነጋግሩ ። ይጠይቁ, **በቤት ውስጥ ልታጋራቸው የሚትችላቸውን አንዳንድ መንገዶች ምንድናቸው?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሳምንት 4


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 አጠቃላይ እይታ



## የኪነ-ጥበብ እና የቀለም ግምገማ

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ ይህንን ያደርጋል:

በቀለም ሙከራዎችን ያደርጋል ፣ ተመሳሳይ የድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላትን ይለያል እና እስከ 5 የሚደርሱ ነገሮችን ይቆጥራል ።

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



## ኪነ-ጥበብ

ነገሮችን ለመወከል ወይም ሀሳቦችን ለመግለጽ ቀለም ቅብ ፣ ሥዕል ፣ ቅርፃ ቅርፅ ፣ ወዘተ



## አርቲስት

እንደ ሥዕሎች ያሉ ኪነ-ጥበቦችን የሚሠራ ሰው ወይም በሰዎች ፊት የሚተውን ሰዉ እንደ ዳንሰኞች እና ዘፋኞች



## የቀለም ብሩሽ

ቀለም ለመቀባት የሚጠቀሙበት ነገር


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት እንደ ቀለም ብሩሽ የተለያዩ ነገሮችን ይጠቀማሉ። ፓኬቱን ከመጀመርዎ በፊት እንደ ቀለም ብሩሽ ሊጠቀሙበት ስለሚፈልጉት ነገር ይጻፉ እና ይሳሉ ።

አስብበት!


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ



## STEM: Finger Counting

- ልጅዎ በጣቶቹ እንዲቆጥር ያስተምሩት። ይህን ይበሉ፣ **በጣቶቻችን እንቁጠር።** እጆትን ጨብጠው ያሳዩት እና ይህን ይበሉ፣ **ወደላይ የተዘረጉ ጣቶች የሉም ማለት ዜሮ ማለት ነው ።**
    - **1** - ጠቋሚዎን ጣትዎን ያውጡ
    - **2** - ጠቋሚውን እና የመሃል ጣትዎን ያውጡ
    - **3** - ሶስቱን የመሃል ጣቶችዎን ያውጡ
    - **4** - አራት ጣቶችዎን ያውጡ (አውራ ጣት አይደለም)
    - **5** - ሁሉንም ጣቶች ያውጡ እና አውራ ጣትንም
- ይህን ይበሉ, **አሁን ከኔጋ ቁጠር።** በጋራ አንድ ጊዜ ያህል በጣትዎ ይቁጠሩ።
- ይጠይቁ, **3 ጣቶችን ልታሳየኝ ትችላለህ?** የትኛውንም 3 ጣቶች በያሳይዎ ምንም ችግር የለውም። ለ 4 ጣቶችም ይድገሙ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ ቴፕ እና ቀለም

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፓሌት, ቴፕ, ወረቀት**

- ይህን ይበሉ, **ቀለም እና ቴፕ በመጠቀም ስዕል መስራት ይችላሉ ። በመጀመሪያ ፣ በወረቀትዎ ላይ በቴፕ አንድ ንድፍ ይስሩ ። ከዚያ ፣ ወረቀትዎን ቀለም ይቀቡ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ በቴፕ እንዲሠራ እና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ቴፕ ስላላቸው የወረቀትዎ ክፍሎች ምን አስተዋልክ?** (ቴፑ የንድፉ አንድ አካል ነው) **።**
- *አማራጭ - ቀለሙ ከደረቀ በኋላ ቴፑን ማውጣት እና የተሰራውን አዲስ ዲዛይን ማየት ይችላሉ።*


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 16

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: **Pat-A-Cake / ፓት - ኧ - ኬክ**

**ቁሳቁሶች**: [Pat-A-Cake / ፓት - ኧ - ኬክ]





- ተመሳሳይ የድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላት ማዳመጥን ተለማመድ። ይህን ይበሉ, **ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች የመጨረሻዎቹ ፊደሎቻቸው ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ አላቸው፣ እንደ pet/ፔት እና net/ኔት። አንድ ግጥም እናንብብ እና ተመሣሣይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላቶች /ራይሚንግ ወርድስ እናዳምጥ ።**
- በጋራ, ግጥም አንብቡ። ይህን ይበሉ፣ **መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው አንዳንድ ቃላቶች ስምቻለው። Bake/ ቤክ እና cake/ ኬክ**
- ግጥሙን ቀስ ብለው እንደገና ያንብቡ። ይጠይቁ, **ምን አይነት ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች ሰምተሃል?** (bake/ቤክ-cake/ ኬክ, man/ማን-can / ካን, b/ቢ-me/ሚ)። ልጅዎ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ቃላትን ለመለየት የሚቸግረው ከሆነ ፣ ችግር የለውም። አሁንም እየተማረ ነው! ቃላቱን ለይለት።

## አንብብ: ***(Rafael's Alley)*** የራፋኤል አሌይ

**ቁሳቁሶች**: [*(Rafael's Alley)* የራፋኤል አሌይ]

- ከልጅዎ ጋር በጋራ, አንብቡ *(Rafael's Alley)* የራፋኤል አሌይ
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **Rafael/ራፋኤል እና Molly /ሞሊ አንዳቸው ለአንዳቸው ራሳቸውን አስተዋወቁ ። ያ ማለት ስማቸውን እርስ በእርስ ተናገሩ ። እራሳችንን ማስተዋወቅ እንለማመድ። ሰላም ስሜ _______ ነው። ስምህ ማን ይባላል?**




የራፋኤል አሌይ
ፅሁፍ እና ምስል በሊቪ ትራሲክ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ፓት - ኧ - ኬክ



ፓት - ኧ - ኬክ, ፓት - ኧ - ኬክ
ቤካርስ ማን

ቤክ ሚ ኧ ኬክ ኣስ ፋስት ኣስ ዩ ካን
ፕሪክ ኢት ኤንድ ፓት ኢት ኤንድ
ማርክ ኢት ዊዝ ኤ “ ቢ “



ኤንድ ፑ ኢት ኢን ዘ ኦቭን
ፉር ቤቢ ኤንድ ሚ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 17

## STEM: የውሃ ቀለም ከለር ቀለም እና ዘይት

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ፣ ትንሽ ማንኪያ ፣ እንደ የወይራ ዘይት ወይም የአትክልት ዘይት እንደ የወይራ ዘይት ፣ ወረቀት**

- ወረቀቱን በሳጥኑ ውስጥ ያስቀምጡ ፣ ጋዜጣ ይዘርጉ ፣ ወይም ቤቱ እንዳይዘበራረቅ ውጪ ወጥተው እንቅስቃሴ ያድርጉ ፡፡
- ይህን ይበሉ, **በውሃ ቀለሞች እና በዘይት ስነ-ጥበባት ስንሠራ ምን ሊሆን እንደሚሆን እንደሚችል እንመልከት።**
- ልጅዎ በውኃ ቀለሞቹ ቀለም መቀባት ይችላል ከዚያም ትንሹን ማንኪያ በመጠቀም ትንሽ ጠብታ ዘይት ይጨምር ፡፡
- በኋላ, ይጠይቁ, **ዘይቱን ሲጨምሩ ስዕልዎ ምን ሆነ?** ለጥቂት ሰዓታት እንዲደርቅ ይተዉት እና የደረቀውን ሥዕል ምን እንደሚመስል ይናገሩ ፡፡

## እራሱን የቻለ ትምህርት፡ የተለያዩ የቀለም ብሩሽዎች

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ፣ ወረቀት ፣ የ"ቀለም ብሩሽ" ሊሆኑ የሚችሉ የቤት ቁሳቁሶች እንደ የቅጠል ቅርንጫፎች ፣ ስፖንጅዎች ፣ ጥጥ**


- ይህን ይበሉ, **ዛሬ የተለያዩ "የቀለም ብሩሽዎችን" መጠቀም ይችላሉ ፡፡**
- ልጅዎ በተለያዩ የቀለም ብሩሽዎች እንዲስል ያበረታቱ ፡፡
- በኋላ, ይጠይቁ, **በተለያዩ የቀለም ብሩሽዎች ስትስል ምን አስተዋልክ? የኪነ-ጥበብ ስራው ለምን የተለየ ይመስልሃል?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 17

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የተዋሃዱ ቃላት አራት



**ቁሳቁሶች**: [የተዋሃዱ ቃላት 4]

- ይህን ይበሉ, **አንድ የተዋሃደ ቃል ለመስራት ሁለት ቃላትን በአንድ ላይ ማሰባሰብን እንለማመድ!**
- ለ "rattlesnake / ራትልስኔክ" ለልጃ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: rattle/ራትል** (ለአፍታ አቁም) **snake/ስኔክ። እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው የራትልስኔክ ሥዕሉን ያሳዩ) **rattlesnake /ራትልስኔክ!**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **rattle/ራትል** (ለአፍታ አቁም) **snake/ስኔክ ።** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የራትልስኔክ ሥዕሉን ያሳዩ ። **rattlesnake /ራትልስኔክ! ታላቅ ስራ!**
- ለነዚህ ቃላቶች ይድገሙ: starfish/ ስታርፊሽ እና rainbow/ ሬንቦ። ልጅዎ 2ቱ ቃላቶች የፈጠሩትን የተቀናጀ ቃል እንዲነግርዎ እንዲሞክር ያድርጉ ። እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም! አሁንም እየተማረ ነው!
  ሌሎቹን ስዕሎች በዚህ ሳምንት ወደ በኋላ ለሚገኘው እንቅስቃሴ ይሆኑ ዘንድ ያስቀምጧቸው።

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ ኪነ-ጥበብ እርምጃ

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የኪነ-ጥበብ የእግር ጉዞ ጆርናል ገፅ**

- ከልጅዎ ጋር በእግር ጉዞ ላይ ሊያዩዋቸው ስለሚችሏቸው የተለያዩ ስነ-ጥበባት ይናገሩ ።
- በእግር ጉዞዎ ማየት ስለሚፈልጉት ኪነ-ጥበብ ልጅዎ ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **በእግር ጉዞ ላይ ማየት ስለምትፈልገው የኪነ-ጥበብ አይነት ንገረኝ ።**


ስም: _______________

በእግር ጉዞ ላይ ምን ዓይነት ጥበብን ማየት ይፈልጋሉ?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።



ራትል



ስኔክ



ራትልስኔክ



ስታር



ፊሽ



ስታርፊሽ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።



ቼር



አርም




አርምቼር



ቦው



ሬን



ሬንቦ



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።



ዊል



ቼር



ባስኬ
ት



ቦል



ዊልቼር



ባስኬትቦል


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: ________________

በእግር ጉዞ ላይ ምን ዓይነት ጥበብን ማየት ይፈልጋሉ?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 18

## **STEM: 5** ነገሮችን እንቁጠር

**ቁሳቁሶች: የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች እንደ ከለሮች ወይም የወረቀት ክሊፖች**

- ይህን ይበሉ, **አንድ ላይ እንቁጠረው ።**
- ሲቆጥሩ 5 ነገሮችን ወደታች ያኑሩ እና እያንዳንዱን ነገር ይንኩ። ይህን ይበሉ **፣ 1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 ፣ 5 ። 5 ነገሮች አሉ።**
- በ 1 እና 5 መካከል መካከል ያሉ ነገሮች ያሳዩት እና ልጅዎ እንዲቆጥራቸው ይጠይቁት። ከዚያ ይጠይቁ, **ሁሉም በአንድ ላይ ስንት ናቸው?** ድምሩን / የመጨረሻውን ሳይናገር እንደገና ቢቆጥር ፣ የተናገው የመጨረሻው ቁጥር የነገሮችን አጠቃላይ /ድምር ቁጥር እንደሚወክል ልጆ እንዲገነዘብ መርዳት ይችላሉ ። **___ ነገሮች አሉ ።**

## እራሱን የቻለ ትምህርት፡ የኔ

**ቁሳቁሶች: የውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች ፣ ወረቀት**

- ይህን ይበሉ, **ሁለተኛ ቀለሞች የሚሠሩት የመጀመሪያ ቀለሞችን በማቀላቀል እንደሆነ ተምረናል ። ሌሎች ቀለሞችን አንድ ላይ ስታቀላቅል እንደገና ሌሎች ቀለሞችን ማግኘት ትችላለህ!**
- **የራስዎን ቀለም ለመፍጠር ቀለሞችን በአንድ ላይ መቀላቀል ይችላሉ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ የግሉን ቀለም እንዲሠራ፣ ቀለሞችን እንዲቀላቀል ያድርጉ ።
- በኋላ ፣ ይጠይቁ ፣ **ስለ ቀለምህ ንገረኝ ። ቀለምህን ለመሥራት ምን ምን ቀለሞችን ቀላቀልክ? የቀለምህ ስም ምን ይባላል?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 18

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: ቲውንክል, ቲውንክል, ሊትል ስታር

**ቁሳቁሶች**: (Twinkle, Twinkle Little Star )
ቲውንክል, ቲውንክል, ሊትል ስታር





- ተመሳሳይ የድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላት ማዳመጥን ተለማመድ። ይህን ይበሉ, **ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች የመጨረሻዎቹ ፊደሎቻቸው ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ አላቸው፣ እንደ skip/ ስኪፕ እና flip/ ፍሊፕ። አንድ ግጥም እናንብብ እና ተመሣሣይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸውን ቃላቶች /ራይሚንግ ወርድስ እናዳምጥ ።**
- በጋራ, ግጥም አንብቡ። ይህን ይበሉ፣ **መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው አንዳንድ ቃላቶች ስምቻለው። Star/ስተር እና are/አር**
- ግጥሙን ቀስ ብለው እንደገና ያንብቡ። ይጠይቁ, **ምን አይነት ራይሚንግ/ተመሳሳይ ድምፅ አወጣጥ ያላቸው ቃላቶች ሰምተሃል?** (star /ስተር-are/አር, high/ሃይ-sky/ ስካይ)። ልጅዎ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ቃላትን ለመለየት የሚቸግረው ከሆነ ፣ ችግር የለውም። አሁንም እየተማረ ነው! ቃላቱን ለይለት።

## አንብብ: ***(Rafael's Alley)*** የራፋኤል አሌይ

**ቁሳቁሶች**: *(Rafael's Alley) የራፋኤል አሌይ*

- በጋራ ከልጆ ጋር, አንብቡ *(Rafael's Alley)* የራፋኤል አሌይ
- በኋላ, በመስኮት ወደ ውጭ ይመልከቱ ወይም አብረው በእርምጃ ይጓዙ ። ስለምታዩት የተለያዩ "ኪነ- ጥበብ" ተነጋገሩ።




የራፋኤል አሌይ
ፅሁፍ እና ምስል በሊቪ ትራሲክ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ረቡዕ

PK3 **ክፍል** 4 **ሣምንት** 4 **ቀን** 18

## እንቀሳቀስ: የለበስከው ልብስ ከሆነ...

**ቁሳቁሶች**: ***አማራጭ - ሙዚቃ***

- ይህን ይበሉ, **ጨዋታ እንጫወት። የሆነ የቀለም አይነትን ከለበሱ ሊያደርጉዋቸው የሚችሉትን የተለያዩ ድርጊቶችን እጠራለሁ ፣ ስለዚህ ያንን ቀለም ለብሰው ከሆነ ያዳምጡ።**
- የተለያዩ ድርጊቶችን ይዘዙ፣ ለምሳሌ ፣ አረንጓዴ ባርኔጣ /ኮፍያ ከለበስክ በእጅህ አጨብጭብ ፣ ወይም ሰሚያዊ ሸሚዝ ከለበስክ በአንድ እግርህ እንካሴ ዝለል።
- ሚናዎችን ይቀይሩ እና ልጅዎ የተለያዩ ድርጊቶችን እንዲያዝ ይፍቀዱለት።

## በጋራ መማር: እንደንስ

**ቁሳቁሶች**: **የልጅዎ እና የእርስዎ ተወዳጅ ሙዚቃ / ዘፈን**

- ይህን ይበሉ, **መደነስ አንዱ የኪነ-ጥበብ አይነት ነው ። የምንወደውን ዘፈን እንጫወት እና የምንወደውን የዳንስ እንቅስቃሴ አንዳችን ላንዳችን እናስተምር!**
- ተራ በተራ ሙዚቃን ለመጫወት እና የዳንስ እንቅስቃሴዎቹን ሌላኛውን ወገን እንዲቀዳ ያስተምራሉ ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ቲዊንክል, ቲዊንክል, ሊትል ስታር

ቲዊንክል, ቲዊንክል ሊትል ስታር
ሃው አይ ዋንዳር ዋት ዩ አር.



አኘ ላብ ዘ ወርልድ ሶ ሃይ
ላይክ ኧ ዲያመንድ ኢን ዘ ስካይ



ቲዊንክል, ቲዊንክል ሊትል ስታር
ሃው አይ ዋንዳር ዋት ዩ አር.


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ



## STEM: የመርጨት ቀለም ቅብ

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, የውሃ ቀለም ፓሌት, የጥጥ ኳሶች ፣ ስፖንጅ ወይም ባለፀጉር የወረቀት ፎጣ ፣ ጋዜጣ ወይም ትሪ**

- ከቤት ውጭ እንቅስቃሴውን ያካሂዱ ወይም ቆሻሻውን ለመያዝ ጋዜጣ ወይም ትሪ ይጠቀሙ ።
- ይህን ይበሉ, **ይህንን የጥጥ ኳስ / ስፖንጅ / የወረቀት ፎጣ ቀለም ከቀባን እና ከተለያዩ ከፍታዎች ወደ ወረቀታችን ብንጥል ምን እንደሚሆን እንመልከት ።**
- ጥጥውን ወደ ቀለሙ ውስጥ እንዴት እንደሚነክሩ ምሳሌ/ሞዴል ሆነው ያሳዩ ከዚያም ወደ ወረቀቱ ላይ ይጣሉት ። ከተለያዩ ከፍታዎች ላይ ልጅዎ እንዲሁ እንዲያደርግ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **በጣም ከፍ ካለ ስፍራ ላይ ጥጡን ስንጥል ምን አስተዋልክ? ወደ ወረቀቱ ቀርበን ስንጥለውስ? ለምን ይመስልሃል?**

## እራሱን የቻለ ትምህርት: ቴክስቸር /ሸካራነትን ማሸትት

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ከለሮች, እንደ ቅጠል ፣ ስፖንጅ ፣ ወዘተ ያሉ ቴክስቸር /ሸካራነት ያላቸው የቤት ቁሳቁሶች**

- ይህን ይበሉ, **በተለያዩ ቴክስትሮች /ሸካራዎች ኪነ-ጥበብን መስራት ይችላሉ ።** ወረቀቱን በቅጠሉ ላይ እንዴት እንደሚያስቀምጥ ለልጁ ያሳዩት እና በቀስታ ይሹት ( የ crayon ን ወረቀት ከላዩ ላይ መላጥ ይችላሉ) በወረቀቱ ላይ የቅጠሉን ቴክስቸር / ሻካራነት እና ቅርፅ ለማግኘት ።
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ቴክስቸር ለማግኘት ማሻሸትን እንዲፈፀም ያድርጉ። በበርካታ ዕቃዎች ላይ መተግበር ይችላሉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ቅጠሉን እያሻሸህ እያለ ምን ተሰማህ?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

# ሐሙስ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 19


## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የእኔ እርምጃዎችን ይግለጹ

- ይህን ይበሉ, **ጨዋታ እንጫወት። ባለፈው ጊዜ ይህንን ጨዋታ ስንጫወት እኔ አንድ እርምጃ ስውስድ አንተ ደግሞ እኔ የማደርገውን መግለፅ ነበረብህ ። አሁን ደግሞ ፣ አንዳችን ለሌላው ምን እንደምናደርግ እንነግራለን ፣ ከዚያ ሌላኛው ሰው ይህንን በተግባር ማሳየት አለበት ።**
- ልጅዎ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ቀላል ድርጊቶች በማስመሰል ይግለጹ ፣ ለምሳሌ ፣ መሳቅ ፣ ቀለም መቀባት ፣ ከአንድ ሰው ጋር መነጋገር ፣ ቅርፃቅርፅ መስራት ፣ ወዘተ ።
- ሚናዎችን ይቀይሩ ልጅዎ እርስዎ እንዲያደርጉት አንድ ነገር እንዲገልፅ ያድርጉ።

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ ሌሎችን ማበረታታት

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, ሌሎችን ማበረታታት ጆርናል ገፅ**

- ከልጅዎ ጋር አንድን ሰው ማበረታታት ስለሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶች ተነጋገሩ ። ይህን ይበሉ, **አንድን ሰው ሲያበረታቱ፣ ያሰዉ የተጨነቀበትን ወይንም ከባድ ሆኖ ያገኘውን ነገር ማድረግ እንደሚችል በመንገር ነው ፣ እንደነዚህ ያሉ አባባሎችን መጠቀም ይችላሉ ፣ ልታደርገው ትችላለህ!**
- ልጅዎ አንድን ሰው ማበረታታት ስለሚችልበት መንገድ ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **አንድን ሰው እንዴት ማበረታታት እንደምትችል ንገረኝ ።**


ስም: ___________________

አንድን ሰው ማበረታታት ስለሚችሉበት መንገድ ይሳሉ እና ይፃፉ ፡፡


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

ስም: ________________

አንድን ሰው ማበረታታት ስለሚችሉበት መንገድ ይሳሉ እና ይፃፉ ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 20

## STEM: ትልቁ የትኛው ነው?

**ቁሳቁሶች: የተለያየ መጠኖች ያላቸው የቤት ዕቃዎች ለምሳሌ ትናንሽ እና ትላልቅ ማንኪያዎች ፣ ትራስ ፣ ካልሲዎች**

- ይህን ይበሉ, **ትልቁን ለማየት እነዚህን ዕቃዎች እናወዳድር ፡፡** ግልጽ የሆኑ የመጠን ልዩነት ያላቸው 2 ነገሮችን ያሳዩ ፡፡ ወደ ትልቁ ነገር አመልክተው፣ **ይህ ከዛኛው ይበልጣል** ይበሉ ፡፡
- ልጅዎ ትልቁን እንዲያመለክተው በመጠየቅ ለ 2-3 ተጨማሪ ጥንድ ይድገሙ ፡፡ ቀለል ለማድረግ ይበልጥ ግልፅ የሆነ የመጠን ልዩነት ያላቸውን ነገሮች ወይም የበለጠ ፈታኝ ለማድረግ ተቀራራቢ መጠን ያላቸውን ነገሮች ይጠቀሙ።
- ልጅዎ እርዳታ ሲያስፈልገው ይርዱት እና አድናቆትዎን መግለፅ እንዳይዘነጉ ፣ **ጥሩ ስራ! በጣም ጠንክረህ እየሞከርክ ነው!**

## እራሱን የቻለ ትምህርት: ቀለምን እና ኪነ–ጥበብን ተሰናበቱ

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ከለሮች**

- ይህን ይበሉ, **እስካሁን ስለ ቀለም እና ኪነ-ጥበብ እየተማርን ነበር ፡፡** ልጅ ስለ ቀለም እና ኪነ-ጥበብ በሚማርበት ወቅት ስለወደደው ክፍል ከልጅዎ ጋር ተነጋገሩ። ስለወደደው እንቅስቃሴ ወይም መጽሐፍ ሊሆን ይችላል።
- ልጅዎ በዚህ ክፍለ- ትምህርት ውስጥ ስለሚወዱት ክፍል ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ፡፡
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **ስለ ምን ነበር የፃፍከው? ለምን ነበር የወደድከው?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።

# አርብ

PK3 ክፍል 4 ሳምንት 4 ቀን 20

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: የተዋሃዱ ቃላት ክለሳ





**ቁሳቁሶች**: [የተዋሃዱ ቃላት 4]() **በዚህ ሳምንት ከዚህ በፊት**

- ይህን ይበሉ, **አንድ የተዋሃደ ቃል ለመስራት ሁለት ቃላትን በአንድ ላይ ማሰባሰብን እንለማመድ!**
- ለ "armchair / አርምቼር" ለልጃ ቁርጥራጮች ያሳዩ። ይህን ይበሉ, **እዚህ ሁለት ቃላት አሉ: arm/ አርም** (ለአፍታ አቁም) **chair/ ቼር። እነዚያን ቃላት በጋራ ከተናገርን ይህንን እናገኛለን** (ቁርጥራጮችን አንድ ላይ አሰባስበው የአርምቼር ሥዕሉን ያሳዩ) **armchair / አርምቼር!**
- **አብረን እንበል,** (ሁለቱን ስዕሎች አሳይ) **arm/ አርም** (ለአፍታ አቁም) **chair/ ቼር ።** ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ያጣምሩ እና የአርምቼር ሥዕሉን ያሳዩ ። **Armchair /አርምቼር! ታላቅ ስራ!**
- ለነዚህ ቃላቶች ይድገሙ: wheelchair/ዊልቼር እና basketball/ባስኬትቦል። ልጅዎ 2ቱ ቃላቶች የፈጠሩትን የተቀናጀ ቃል እንዲነግርዎ እንዲሞክር ያድርጉ ። እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም! አሁንም እየተማረ ነው!

## አንብብ: (*Rafael's Alley*) የራፋኤል አሌይ

**ቁሳቁሶች**: [*(Rafael's Alley) የራፋኤል አሌይ*]()

- በጋራ ከልጃ ጋር, አንብቡ *(Rafael's Alley) የራፋኤል አሌይ*
- በኋላ, ሊፈጥሩት ስለሚፈልጓቸው የጥበብ ዓይነቶች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ። ይጠይቁ, **ምን ዓይነት ኪነ-ጥበብን መፍጠር ትፈልጋለህ? ምን ማድረግ ትውዳለህ?**





የራፋኤል አሌይ

ፅሁፍ እና ምስል በሊቪ ትራሲክ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቨሪ ቻይልድ ሬዲ።

ክፍል 4 በጠቅላላ ስለ ኪነ-ጥበብ እና ስለ ቀለም ነው! ልጅዎ ስለተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዓይነቶች እና ስለ መጀመሪያ እና ሁለተኛ ቀለሞች ይማራል!



AppleTree

©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ኢንስቲትዩት። ኤቭሪ ቻይልድ ሬዲ።